መስከረም 2018

EUROPEAN
INSTITUTE
OF PEACE

# በኢትዮጵያ የሰላም ሂደት ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርስ መገለል ሲፈተሽ፡ የዳራ/የአውድ ጥናት



## ምስጋና

ይህ የዳራ/አውድ ጥናት ሰነድ የአውሮፓ የሰላም ተቋም በጀርመን ፌዴራላዊ የውጭ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ድጋፍ እየመራው ያለው እንቅፋቶችን ማስወገድ፣ ሰላምን ማበጀት የተሰኘ ፕሮጀክት አካል ነው። ጥናቱ ትኩረት የደረገበት ጉዳይም በኢትዮጵያ ውስጥ በስርዓተ ጾታ እና በግጭት መካከል ያለው መስተጋብር በተለይም በሰላም ግንባታ ጥረቶች ላይ ሴቶች እንዴት እና የት ቦታ የመሪነት ሚና እንደተጫወቱ እንዲሁም ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳደረጉ መመርመርን ነው። ግኝቶቹም የሴቶችን ተሳትፎ የሚያሳንሱ ለረጅም ጊዜ የቆዩ እንቅፋቶችን አጉልተው የሚያሳዩ ሲሆን፤ ግጭትን በመከላከል እና በሰላም ሂደቶች ውስጥ ሴቶች ያላቸውን ሚና ለማሳደግ የሚጠቅሙ ተጨባጭ እርምጃዎችንም ያቀርባሉ። እነዚህ ሐሳቦች ደግሞ ገና እያደጉ ያሉ አካባቢያዊ የሰላም ግንባታን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ጭምር የሴቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማሳደግ የሚሆኑ በማስረጃ ላይ የተመሠረቱ ምክረሐሳቦችን ለፖሊሲ አውጪዎች እና ለባለሙያዎች በማስጨበጥ አለም አቀፉን የሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት(WPS) አጀንዳዎች ወደፊት የማስኬድ ግብ ላለው Status Quo or Bold Adaptation? Reclaiming the Women, Peace and Security Agenda (ያለውን ሁኔታ ማስጠበቅ ወይስ ጽኑ ተዋህዶ? የሴቶች ሰላም እና ደህንነት አጀንዳን እንደገና መጠየቅ) _ ለተሰኘው ዓለም አቀፍ ሪፖርት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።
ከዚህ የዳራ ጥናት ሌላ ሁለት Navigating Barriers To Women's Participation in Policy Spaces Intersecting with Environmental Peacebuilding (ከአከባብያዊ ሰላም ግንባታ ጋር በሚገናኝ የፖሊሲ ምህዳር ውስጥ ለሴቶች ተሳትፎ እንቅፋት የሆኑትን መ ቃኘት)እንዲሁም Reclaiming the Women Peace and Security Agenda in Sudan: A Background Paper (በሱዳን የሴቶች ሰላምና ደህንነት አጀንዳን መመለስ: መሰንዘሪያ ሰነድ) (መሰረታዊ ሰንድ) የሚሉ ርእሶች ያሏቸው ጥናቶች ተዘጋጅተዋል። እነዚህም ጥናቶች Status Quo or Bold Adaptation? Reclaiming the Women, Peace and Security Agenda (ያለውን ሁኔታ ማስጠበቅ ወይስ ጽኑ ተዋህዶ? የሴቶች ሰላም እና ደህንነት አጀንዳን እንደገና መጠየቅ ) ለተሰኘው ዓለም አቀፍ ሪፖርት ግኝቶች እንደግብዓት አገልግለዋል።
እነዚህ ጥናቶች የሚወጡበትን ጊዜ ልዩ የሚያደርገው አለም አቀፉ ማህበረሰብ የሴቶች፣ የሰላም እና ደህንነት አጀንዳን 25ኛ ዓመት መታሰቢያ ለማክበር እየተቃረበ ባለበት ሰዓት የተዘጋጁ መሆናቸው ነው። ይህም ምእራፍ ወደኋላ መለስ ብሎ ጉዳዩን መመርመርን እና ቁርጠኝነትን ማደስን የሚጋብዝ ነው። Practices for Inclusive Peace: A Practitioner's Compendium of Resources (ለአካታች ሰላም የሚበጁ ልምምዶች፡ የባለሙያዎች የአሰራር ምንጮች መዝገብ) የተሰኘው ሰነድ እንዲሁም እነዚህ የዳራ ጥናቶች በቦታው ላይ የሚገኙ የሴት ሰላም ገንቢዎችን ተጨባጭ የሕይወት ልምድ፣ እውቀት እና ፈጠራዎች በአለም አቀፍ ፖሊሲዎች ውስጥ የማስገባትን አስፈላጊነት አስረግጠው የሚናገሩ ናቸው። በመጪዎቹ ዓመታትም የተሻለ ምላሽ መስጠት የሚችሉ እና ውጤታማ የሆኑ የሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት ስልቶችን በመቅረጽ ረገድ ድጋፍ የሚያደርጉ ናቸው።

የኢትዮጵያው ሪፖርት አጥኚዎች/አዘጋጆች፡ ስም-አልባ
ስም-አልባ፤ "በኢትዮጵያ የሰላም ሂደት ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርስ መገለል ሲፈተሽ፡ የዳራ/የአውድ ጥናት"

ገምጋሚዎች፡ ሶፊያ ክሎዝ፣ ሲያድ ዳርዊሽ እና ኬት ቢዩካናን
የፕሮጀክት መሪ፡ ሚሪያም ሪፈርሼይድት (የስርዓተ ጾታ እና የሰላም ግንባታ ፕሮግራም መሪ) እንዲሁም ፓዋሊን ቻቪዩ (የስርዓተ ጾታ እና የሰላም ግንባታ ፕሮግራም ኦፊሰር)
የቅጂ አርታኢ፡ ኬሊ ፍሪየል
የግራፊክ ዲዛይኑን የሰራው፡ ዶሮቲ አሊቬሪዩ
ሰአሊ፡ ቪዱቪ ያዳቭ/Studio We are Stories
የነበሩትን ስጋቶች ተቋቁመው ለቃለመጠይቅ ፍቃደኛ ለነበሩት የጥናቱ ተሳታፊዎች ሁሉ ተቋሙ ከልብ የመነጨ ምስጋናውን ያቀርባል።
አስተዋጽኦዎቻቸው ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸው እና ለጥናቱም መሠረታዊ ነበሩ።

ለማንኛውም አስተያየት እባክዎ እነዚህን የኢሜል አድራሻዎች ይጠቀሙ፡ info@eip.org
ጽሑፉ ተደራሽ እና በቀላሉ ተነባቢ እንዲሆን ለማስቻል፤ በመላው ሪፖርቱ ውስጥ በግራ በኩል ቀጥ ያለ ህዳግ እንዲኖረውተደርጓል።

ይህ ሪፖርት በእንግሊዝኛ የተዘጋጀው ዋና ስሪት/ቅጂ ትርጉም ነው፤ ልዩነቶች በሚኖሩበት ጊዜ የእንግሊዝኛው ስሪት/ቅጂ ገዢ ተደርጎ ይወሰዳል።

የዚህን ህትመት ምንጭ በመጥቀስ እውቅና እስከተሰጠ ድረስ ያለ ባለቅጂ መብቱ ልዩ ፍቃድ ህትመቱን በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሁም በማንኛውም ቅርጽ ለትምህርትዊ እና ለትርፍ ለማይውል አላማ አባዝቶ መጠቀም ይቻላል። ከአውሮፓ የሰላም ተቋም በጽሁፍ ፍቃድ ካልተገኘ በስተቀር ይህንን ህትመት ለሽያጭ ወይም ለሌላ ለማናቸው ጥቅም የሚያስገኝ አላማ ማዋል ፈጽሞ አይቻልም።

የአውሮፓ የሰላም ተቋም (2018)

# ማውጫ


1. መግቢያ 4
1.1. የቁልፍ ግኝቶች አጭር መግለጫ 5
1.2. የሪፖርቱ መዋቅር 5

2. ዳራ 6

3. ግኝቶች፡ ሴቶች ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ የሚያግዱ እንቅፋቶች (እና እንዴት መታለፍ እንደሚችሉ) 7
3.1. እንቅፋት 1፡ የጸጥታ እጦት እና እየጠበበ የመጣ የሲቪክ ምህዳር 7
3.2. እንቅፋት 2፡ የፖሊሲ መቆየት እና የተጠያቂነት እጥረት 9
3.3. እንቅፋት 3፡ ገንዘብ ነክ እንቅፋቶች እና ኢኮኖሚያዊ መገለል 11
3.4. እንቅፋት 4፡ ነጻነት ገዳቢ የስርዓተ ጾታ ደንቦች እና ማህበራዊ መገለል 13

4. ማጠቃለያ 16

አባሪ፡ የጥናቱ ሥነዘዴ 17

የጀርባ ማስታወሻዎች 18

## 1. መግቢያ

ይህ የዳራ ጥናት የአውሮፓ የሰላም ተቋም እያከናወነ የሚገኘው እንቅፋቶችን ማለፍ፣ እና ሰላምን የመፍጠር ፕሮጀክት አካል ነው። ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት በተደጋጋሚ በሚፈጠሩ ግጭት ባስከተሉ የፖለቲካ ሽግግር ታሪካዊ ውርሶች እና ከሁሉን አካታች ሰላም ጋር ተይይዞ በሚታይ ጭላንጭል ተስፋ መካከል በሚገኝ ወሳኝ መስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች። ምንም እንኳን በቅርብ ጊዜ የተከናወኑ ማሻሻያዎች ዴሞክራሲያዊ ህዳሴን በተመለከተ ተስፋ ሰጪ የነበሩ ቢሆንም፤ በዚያው ልክ በሀገረመንግሥቱ ሥሪት ውስጥ የሚገኙ ጥልቀት ያላቸው ስንጥቃቶችንም በማጋለጥ በቀጣይነት የሕይወት መጥፋትን እና የማህበራዊ ትስስሮች መሸርሸርን ያመጡ ተደራራቢ የግጭት ማዕበሎችን አስከትለዋል።[1] ወትሮም የመፈናቀሉን፣ የወሲባዊ ጥቃቱን እና የኢኮኖሚውን መቃወስ ገፈት ቀማሽ የሆኑት ሴቶች እና ልጃገረዶች በዚህም ግጭት ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ምላሽ ሰጪዎች እና ተገቢው  ትኩረት ያልተሰጣቸው የግጭቱ ሰለባዎች ሆነዋል። ይሁን እንጂ ሰላምን በመገንባት ረገድ ያላቸው የመሪነት ሚና አሁንም ቢሆን ዋጋ ያልተሰጠው፣ ድጋፍ ያላገኘ እንዲሁም መዋቅራዊ መገለል የሚስተዋልበት ነው። የዚህም ሪፖርት ሐሳብ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚሆን መንገድ መዘርጋት ይቻል ዘንድ ኢትዮጵያ ሴቶችን ማካተት አለባት የሚል ነው። ሴቶችን በዋነኛነት የሰላም ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆን የሰላም ሥራ እቅድ፣ ስትራቴጂ እና አፈጻጸም መሪዎች እንደሆኑ አድርጎ የሰላም ሂደትን እንደገና ማሰብ እንደሚያስፈልግ ጥሪ ያቀርባል።

በኢትዮጵያ በፌደራል እና በክልል ደረጃ በሚገኙ ልሂቃን መካከል የተከሰተው ፖለቲካዊ ውጥረት በበርካታ ክልሎች በተለይም በትግራይ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ውስጥ ወደ መጠነ ሰፊ የትጥቅ ግጭት ተባብሷል። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በፌደራል መንግሥት እና በትግራይ ህዝብ ነጻነት ግንባር መካከል የተካሄደው ጦርነት የተነሳው ፌደራሊዝምን፣ የሥልጣን ክፍፍልን እና የጦር ሠራዊት ቁጥጥርን በተመለከተ በመካከላቸው የነበረው መተማመን በመታጣቱ  ነው። በመገናኛ ብዙኃን እና በእርዳታ ድርጅቶች[2] ላይ በነበረው ከፍተኛ ገደብ ምክንያት የጦርነቱ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ትክክለኛ ቁጥር የማይታወቅ ቢሆንም፤ ሕይወታቸውን ያጡ ሰላማዊ ሰዎች ቁጥር እስከ 600000 እንደሚሆን ይገመታል።[3] በግጭቱ የተሳተፉት ሁለቱም ወገኖች የጦር ወንጀሎችን እና በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ፈጽመዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል።[4]

የሀገሪቱ እምብርት በሆነ አካባቢ ውስጥ የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት (OLA) ከፖለቲካዊ መገለል እና ከክልላዊ ራስገዝነት ጋር በተያያዘ ዘመናትን ባስቆጠረ ቁርሾ ላይ ተመሥርቶ  የተራዘመና የተደረጀ የትጥቅ ትግል   እያካሄደ ይገኛል።[5] በአማራ ክልል ውስጥ በክልላዊ ማንነታቸው፣ በክልላዊ የወሰን አንድነታቸው እንዲሁም ከክልላዊ የጸጥታ ኃይሎች መፍረስ ጋር በተያያዘ እንደተቃጣባቸው ለሚያስቡት ስጋት ምላሽ ለመስጠት የታጠቁ ብሔርተኛ ወጣቶች ቡድኖችን ያካተተው የፋኖ ሚሊሻ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።[6] እነዚህ ተደራራቢ ግጭቶች በሰላማዊ ዜጎች ላይ የደረሰ ከባድ ጉዳትን፣ መፈናቀልን እንዲሁም መጠነ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ መስተጓጎልን አስከትለዋል።[7]

ይህ ጥናት በተጻፈበት ወቅት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሰብአዊነት ቀውሶችን እያስተናገደች ትገኛለች፤ እነዚህም እየተካሄዱ በሚገኙ ግጭቶች ሳቢያ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ከ20 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ሰዎች መኖራቸውን፣ ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ አደጋዎችን እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ አቅርቦት እጥረትን ያካትታሉ።[8] በ2016 የተካሄዱ የሰብአዊ እርዳታ ሥራዎች 11.4 ሚሊዮን ሰዎችን የደረሱ ቢሆንም በእርዳታ ፍላጎት እና አቅርቦት መካከል ያለው ክፍተት አሁንም በጣም ሰፊ ነው።[9] በተጨማሪም ሀገሪቱ ከ1 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ስደተኞችን፤ እንዲሁም በዋነኛነት በትግራይ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል በተከሰቱት ግጭቶች እና በአየር ንብረት ቀውስ ሳቢያ ከፍተኛ የምግብ እጥረት የተጋረጠባቸውን ከ4.5 ሚሊዮን በላይ የሆኑ በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ታስተናግዳለች።[10]

በኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰቱት ግጭቶች በዋናነት  ለጉዳት የተዳረጉት ሴቶች እና ልጃገረዶች ሲሆኑ ይህም መጠነ ሰፊ በሆነ ወሲባዊ እና ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት፣ መፈናቀል እንዲህም በመሠረታዊ አገልግሎቶች መስተጓጎል ይገለጣል። በትግራይ፣ በአማራ፣ በአፋር እና በኦሮሚያ ክልሎች ውስጥ ለ2 አመታት በተካሄደው ጦርነት፤ በግምት ከ40 እስከ 50% የሚገመት መጠን ያላቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች ወሲባዊ እና ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የደረሰባቸው ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 90% የሚሆኑት ከ18 አመት በታች የሆኑ ልጃገረዶች ናቸው።[11] በዚህም የተነሳ በ2013ዓም 3.5 ሚሊዮን የነበረው በመላው ሀገሪቱ የሚገኘው ጾታን መሠረት ካደረገ ጥቃት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር በ2014ዓም ወደ 5.8 ሚሊዮን ከፍ ብሏል።[12] የጤና መሠረተልማቶች መውደማቸውም ቀውሱን የበለጠ ያባባሰው ሲሆን፤ ይህንኑ ተከትሎ በትግራይ የነበረው የኤች አይ ቪ ስርጭት ከእጥፍ በላይ ሆኖ 3% ከመድረሱም በላይ ይህም ቁጥር የተፈናቀሉ ሰዎች እና የወሲባዊ ጥቃት አገጋሚዎች ዘንድ ደግሞ ከዚም በላይ ይጨምራል[13]

ይህ ጥናት ማሳካት የሚፈልገው፡ (1) በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች ግጭትን በመከላከል ረገድ፣ በሰላም ሂደት ውስጥ እንዲሁም በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚያግዷቸውን እንቅፋቶች መግለጥን እንዲሁም (2) እነዚህን እንቅፋቶች ለማለፍ እና የሴቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማጠናከር የተቀመጡ ስትራቴጂዎችን ወይም ተስፋ ሰጪ ልምምዶችን መለየትን ነው። በተጨማሪም ሪፖርቱ በአብዛኛው በየአካባቢው በሚገኙ በሴቶች መብቶች ላይ በሚሠሩ ድርጅቶች አስቀድመው በተከናወኑ ወሳኝ ትንተናዎች ላይ የሚጨምር እና በአሁኑ ወቅት ሴቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ እና የሰላም ግንባታ ምህዳር ውስጥ ያላቸውን ቦታ የሚተነትን ነው።

## 1.1. የቁልፍ ግኝቶች አጭር መግለጫ

ጥናቱ ሴቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም ግንባታ እና በግጭት አፈታት ረገድ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚያግዷቸውን አራት እርስ በእርስ የተያያዙ እንቅፋቶችን ከመለየቱም በላይ እነዚህንም ለማስወገድ የሚጠቅሙ ኢላማ ተኮር ስትራቴጂዎችንም ያቀርባል። እነዚህን እንቅፋቶች የፈጠሯቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ኢኮኖሚያዊ ገደቦች እና ስር የሰደዱ የስርዓተ ጾታ ደንቦች ሲሆኑ እነዚህም የተቀናጁ ሕጋዊ፣ ገንዘብ ነክ እንዲሁም ማህበረሰብ መር ሥራዎችን በመጠቀም መፈታት ያለባቸው ናቸው።

- እንቅፋት 1፡ የጾጥታ እጦት እና እየጠበበ የመጣ የሲቪክ ምህዳር። ግጭት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ለሚንቀሳቀሱ ሴት የሰላም ገንቢዎች በፀጥታ እጦት ምክንያት ጥቃት እንዳይደርስባቸው የአድራሻ ለውጥ ድጋፍ፣ በዲጂታል የደህንነት መሣሪያዎች እንዲሁም በቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶች አማካኝነት የደህንነት ማስጠበቂያ ስልቶችን መፍጠር እና ማጠናከር። የጦር ሠራዊት የድርድር አመክንዮ ላይ ያልተመሠረቱ አካታች የሰላም መድረኮችን ማስፋት። ከልሂቃን ወይም ከታጠቁ ኃይሎች ውክልና ይልቅ ለአካባቢያዊ ሕጋዊነት ቅድሚያ መስጠት እና ደህንነታቸው የተጠበቀ የዜግነት/ሲቪክ ተሳትፎ መድረኮች ለሴቶች ያላቸውን ተደራሽነት ማረጋገጥ።
- እንቅፋት 2፡ የፖሊሲ መቆየት እና የተጠያቂነት እጥረት ። የኢትዮጵያ የተሻሻለው ብሔራዊ የስርዓተ ጾታ ፖሊሲ እና ሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት ብሔራዊ የድርጊት መርሃግብር የሚጸድቁበትን ሂደት መከታተል እና ማፋጠን። በምርጫ እና በሰላም አስተዳደር ማዕቀፎች ውስጥ የስርዓተ ጾታ ተዋጽኦን ማስረጽ እንዲሁም ይህንኑ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ተቋማትን ተጠያቂ ማድረግ። በሴቶች የሚመሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የቁጥጥር ሚናን እንዲወጡ መደገፍ እንዲሁም በፌደራል እና ክልላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች ውስጥ ሁሉ ሴቶች ሰላም እና ጸጥታ (WPS) ውሳኔዎችን በተመለከተ ሕጋዊ ኃላፊነቶችን ማቋቋም።
- እንቅፋት 3፡ ገንዘብ ነክ እንቅፋቶች እና ኢኮኖሚያዊ መገለል። ከሰላም ግንባታ ጋር የተያያዙ መሠረታዊ እና ለአፈጻጸም ምቹ የሆነ የገንዘብ አቅርቦት፣ የሙያ ሥልጠና እንዲሁም ገቢ የማመንጫ እድሎች ለሴቶች ያላቸውን ተደራሽነት ማየት እና ማስፋፋት። በየአካባቢው የሚገኙ ሴቶች በውይይት ሂደቶች ላይ መሳተፍ ይችሉ ዘንድ አበል/ድጎማ፣ የሕጻናት ማቆያ አገልግሎትን እና ሎጂስቲካዊ ድጋፍን ማቅረብ። የለጋሾች ስትራቴጂዎች ከሰብአዊነት፣ ከልማት እና ከሰላም መርሆች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ዘላቂነት ባላቸው እና በመተማመን ላይ በተመሠረቱ አጋርነቶች አማካኝነት በሴቶች የሚመሩ ድርጅቶችን መደገፍ።
- እንቅፋት 4፡ ነጻነትን የሚገድቡ የስርዓተ ጾታ ደንቦች እና ማህበራዊ መገለል። ሴቶችን ከባህላዊ እና መደበኛ/ሕጋዊ የሰላም ሂደቶች የሚያገሉ ስር የሰደዱ አባዊ እምነቶችን መፈተሽ እና መገዳደር። የሴቶችን የመሪነት ሚና ከፍ ለማድረግ በማህበረሰብ አቀፍ የግንዛቤ ዘመቻዎች፣ የስርዓተ ጾታ ለውጥ በሚያመጣ ትምህርት እንዲሁም በትውልዶች መካከል በሚካሄዱ ውይይቶች ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን መሥራት። በየአካባቢው ተመሥርተው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ስርዓቶችን ጨምሮ ነባር ማህበራዊ መዋቅሮችን በመጠቀም በልማዳዊ ደንቦች ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚሠሩ የሴታዊት ድርጅቶችን ማሳደግ።

## 1.2 የሪፖርቱ መዋቅር

አግባብነት ካላቸው ኢትዮጵያውያን ባለድርሻዎች ጋር በተደረጉ ምክክሮች ላይ በመመስረት ሴቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማድረግ የቻሉት የት እና እንዴት እንደነበር በሚያሳዩ መረጃዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ሪፖርቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በስርዓተ ጾታ እና በግጭት መካከል ያለውን መስተጋብር ይመረምራል (ክፍል 2)። የግኝቶቹም አላማ የሴቶችን ተሳትፎ የሚያግዱ እንቅፋቶችን መዘርዘር እና እንዲወገዱ ለማድረግ የሚረዱ ግልጽ ተግባራትን ማስቀመጥ ነው (ክፍል 3)። እንቅፋቶቹም በኢትዮጵያ ውስጥ ግጭትን በመከላከል እና በሰላም ሂደት ረገድ ሴቶች የሚያደርጉትን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማጠናከር ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን የሚዘረዝሩ ምክረ ሐሳቦችን ያካትታሉ። አባሪዎቹ ደግሞ የጥናቱን ሥነዘዴ ይገልጻሉ።

## 2. ዳራ

ለእነዚህ ቀውሶች ምላሽ ለመስጠት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሰላም ግንባታ ሥራዎችን ጀምረዋል፤ እነዚህም ሥራዎች ስር የሰደዱ ቁርሾዎችን የመፍታት እና ግጭቶች የሚለወጡበትን መንገድ የማመቻቸት አላማ ያላቸው የውይይት መድረኮችን መፍጠርን ያካትታሉ። የኢትዮጵያ መንግሥትም ሁለት ተመጋጋቢ ስትራቴጂዎችን አስቀምጧል፡ እነዚህም ብሔራዊ የምክክር ሂደት እና በቀጥታ ከታጠቁ ቡድኖች ጋር መደራደር ናቸው። ብሔራዊ ምክክሩ መዋቅራዊ የግጭት መንስዔዎችን ለመፍታት የተቀረጸ ሲሆን ድርድሮቹ ደግሞ በእንቅስቃሴ ላይ ካሉ አማጽያን ጋር ፖለቲካዊ ስምምነትን ማምጣት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህንንም ሂደት ለመምራት መንግሥት ጥር 14 ቀን 2014 ዓም 11 አባላት ያሉትን ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽንን ያቋቋመ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ሶስቱ ብቻ ሴቶች ናቸው። ከዚሁ ትይዩ መንግሥት ከትህነግ እና ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር ይፋዊ ድርድሮችን አካሂዷል።

ምንም እንኳን ሴቶች ከበፊቱም በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሽግግሮች ውስጥ ቁልፍ ተዋናዮች ሆነው የቆዩ ቢሆንም የመሪነት እና የሰላም ገንቢነት ሚናቸው ዘላቂነት ያለው ፖለቲካዊ አቅምን ሊፈጥር አልቻለም። ከ1966ቱ አቢዮት እስከ 1983ቱ የመንግሥት ለውጥ ብሎም እስከ 2010ሩ ማሻሻያ፤ ሴቶች በሰላማዊ ተቃውሞ እንዲሁም በትጥቅ ትግልም ውስጥ ተሳትፈዋል። በውሳኔ ሰጪነት ምህዳር ውስጥ ያላቸው ውክልና አነስተኛ ሆኖም እንኳን፤ ማህበረሰብን በማንቃት፣ መደበኛ ድርጅቶችን በማደራጀት እንዲሁም በነጻነት ትግሎች ውስጥ በመሳተፍ ባደረጉት እንቅስቃሴ፤ ሴቶች ፖለቲካዊ ውጤቶች ላይ አሻራቸውን ማሳረፍ ችለዋል።[15]

በ2010 በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ መሪነት የተካሄደው ማሻሻያ በሴቶች የፖለቲካ ውክልና ታሪክ ውስጥ ወሳኝ እጥፋት ሆኖ ተመዝግቧል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተዳደር የጾታ እኩልነት ያለውን ካቢኔ ከማስተዋወቁም በላይ፤ የመጀመሪያዋን ሴት ርእሰ ብሔር የሾመ ሲሆን እንዲሁም በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የበላይ ኃላፊነት ቦታዎችም ላይ ሴቶችን ሾሟል።[16] እነዚህ ምሳሌነት ያላቸው ምዕራፎች በፖለቲካዊ ስርዓቱ ላይ የስርዓተ ጾታ ለውጥ ይመጣል የሚል ተስፋን አሳድሯዋል። በ2011 በተካሄደ ብሔራዊ የሰላም ጉባዔ ላይ የተገኙ ሴት አመራሮች ለሰላም ያላቸውን የጋራ ቁርጠኝነት ከማረጋገጣቸውም በላይ የሴቶችን ድምጽ ለማጉላት ምክር፣ ቅንጅት እና መደጋገፍ እንደሚያስፈልግ ጥሪ አቅርበዋል።[17] እንደሶማሊ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባሉ አንዳንድ አካባቢዎች የሴቶች በአመራር ቦታዎች ላይ መሾም የህብረተሰቡን አስተሳሰብ የቀየረ ከመሆኑም ባሻገር ለአካባቢያዊ ውይይቶች እንዲሁም ስር የሰደዱ የስርዓተ ጾታ ደንቦችን ለመፈተሽ እድሉን ከፍቷል።[18] ይሁን እንጂ፤ ትርጉምያለው ለውጥ እንዲመጣ ዘላቂነት ያለው የፖለቲካ ፈቃደኝነት፣ አካታች የሰላም ሂደት እንዲሁም ከውክልና ባሻገር ሴቶችን በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማሳተፍ ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች በሴቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ቢያሳድሩም፣ የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት (WPS) አጀንዳ በመደበኛ የሰላም ሂደቶች ውስጥ እዚህ ግባ የሚባል ቦታ የለውም። ለምሳሌ፣ በህዳር 2014 የትግራይን ግጭት ባስቆመው የፕሪቶሪያ ስምምነት ሂደት ውስጥ እንደ ዋና ተደራዳሪ ወይም አስታራቂ ሴቶች አልተካተቱም።[19] በተመሳሳይ፣ በማኅበረሰብ ላይ የተመሠረተ የሰላም ግንባታን በማራመድ ረጅም ታሪክ ያላቸውን ጨምሮ፣ በየአካባቢው ያሉ የሴቶች ድርጅቶች ከመደበኛ ምክክር እና አጀንዳ አወጣጥ ሂደት በአብዛኛው ተገልለዋል።[20] በሚያዚያ 2014 እና ኅዳር 2015 በፌዴራል መንግሥት እና በኦነግ መካከል በዳሬሰላም፣ ታንዛኒያ በተከታታይ የተደረገው ድርድርም የሴቶች ተሳትፎ አልነበረውም። ከሁለተኛው ዙር በፊት፣ ከኦሮሚያ እና ከመላው አገሪቱ የተውጣጡ ሴት የሰላም አስፈጻሚዎች የግጭቱን የጾታ ልዩነት ላይ ያተኮረ ተፅዕኖ ማለትም መፈናቀልን፣ ጾታዊ ጥቃትን እና አለመረጋጋትን በማንሳት እንዲካተቱ በይፋ ቢጠይቁም፣ ዳግም ከሂደቱ ውጪ ሆነዋል።[21] በጥር 2016 በኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት እና በቀድሞ የኦነግ አዛዥ መካከል የተደረገው ክልላዊ የሰላም ስምምነትም ሴቶችን አላካተተም።[22]

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 1325 ፈራሚ ስትሆን የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት (WPS) አጀንዳን ተግባራዊ ለማድረግ ቃል ገብታለች። ሆኖም ተቋማዊ ማዕቀፎቿ አሁንም በቂ አይደሉም። አሁን ያለው ሕግ በግጭት ወቅት የሚከሰቱ የጾታ ልዩነቶችን ያካተቱ ተጽእኖዎችን ለመፍታት፣ ሴቶች በሰላም ሂደቶች ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማረጋገጥ ወይም በሰብአዊ እና ከግጭት በኋላ ባሉ ሁኔታዎች ጥበቃን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች የሉትም።[23] የተባበሩት መንግሥታት የሴቶች ድርጅት (UN Women) እና የኢትዮጵያ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ከ2011 ጀምሮ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር (NAP) ለማዘጋጀት ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ ቢሆንም ነገር ግን ትግበራው ውስን ነው።[24]

በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች ሰላምንና ደህንነትን ለማስፈን ካደረጉት ተከታታይ አስተዋጽኦ መካከል እንደ አደራጅች፣ የሰላም አስከባሪዎችና ተደራዳሪዎች የሠሩት ሥራ የሚጠቀስ ነው። ሆኖም አባዊነትን መሠረት ያደረጉ ደንቦችና ተቋማዊ እንቅፋቶች ድምፃቸውን በማዳፈን ላይ ናቸው። የሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ አስቸኳይ ማሻሻያ ካልተደረገ የሰላም ሂደቶች ሁሉን አቀፍና ዘላቂ ሊሆኑ አይችሉም። ከዚህም በተጨማሪ ሴቶችን ማግለል የሴቶችን ፍላጎቶችና ግጭትን በመፍታትና በማገገም ረገድ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ የማበርከት አቅማቸውን ችላ ማለት ነው። የሴቶች፣ ሰላምንና ደህንነት አጀንዳን በኢትዮጵያ ብሔራዊና ክልላዊ የሰላም ሂደቶች ውስጥ ማስገባት የፍትህ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁሉን አቀፍ ሰላም ግንባታ ስልታዊ ግዴታ ነው።

# 3. ግኝቶች፡ ሴቶች ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ የሚያግዱ እንቅፋቶች (እና እንዴት መታለፍ እንደሚችሉ)

በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ጉልህ መሻሻሎች ቢኖሩም፣ ውስብስብ የፖለቲካ፣ የጸጥታ እና የፖሊሲ ነክ እንቅፋቶች ሴቶች በሰላም ሂደቶች ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ ማስተጓጎላቸውን ቀጥለዋል። እየተካሄዱ ያሉ የትጥቅ ግጭቶች፣ በመንግሥት ተቋማት ላይ ያለው አለመተማመን፣ የስርዓተ ጾታን ያላገናዘቡ ፖሊሲዎች እና እየጠበበ የመጣው የሲቪክ ምህዳር ለሴት ሰላም ገንቢዎች አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል። የሕግ ጥበቃ፣ ሁሉን አቀፍ ፖሊሲዎች ወይም ደህንነታቸው የተጠበቀ የሥራ ሁኔታዎች ከሌሉ፣ ሴቶች ለሰላምና እርቅ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ውስን፣ ዋጋ የማይሰጠው እና ብዙ ጊዜ ወደ ጎን የሚገፋ ሆኖ ይቀራል። ይህ ክፍል እነዚህ መዋቅራዊ ተግዳሮቶች እንዴት እንደሚገናኙ የሚዳስስ ሲሆን የሀገሪቱን የሴቶች፣ ሰላምና ደህነት (WPS) አጀንዳ ለማሳደግ መታረም ያለባቸውን አስቸኳይ ክፍተቶች ይለያል።

- እንቅፋት 1፡ የጸጥታ እጦት እና እየጠበበ የመጣ የሲቪክ ምህዳር
- እንቅፋት 2፡ የፖሊሲ መቆየት እና የተጠያቂነት እጥረት
- እንቅፋት 3፡ ገንዘብ ነክ እንቅፋቶች/እጥረት እና ኢኮኖሚያዊ መገለል
- እንቅፋት 4፡ ነጻነት ገዳቢ የስርዓተ ጾታ ደንቦች እና ማህበራዊ መገለል

## 3.1 እንቅፋት 1፡ የጸጥታ እጦት እና እየጠበበ የመጣ የሲቪክ ምህዳር

የብሄር ፖለቲካ፣ የታጣቂዎች መበራከትና የመንግሥት ህጋዊነት መዳከም በኢትዮጵያ ሴት ሰላም ገንቢዎች ተሳትፎ የሚያደርጉበትን የሲቪክ ምህዳር እያጠበበው ነው። የትግራይን ጦርነት፣ በኦሮሚያ የሚካሄደውን አመፅና በአማራ ክልል ያለውን አለመረጋጋት ጨምሮ ግጭቶች ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ የፖለቲካው ምህዳር በየጊዜው ወታደራዊ ገጽታ እየተላበሰ መጥቷል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ታጣቂ ቡድኖች መበራከት፣ መንግሥት በኃይል አጠቃቀም ላይ የነበረውን ብቸኛ የበላይነት ማጣቱና በዜጎችና በመንግሥት መካከል ያለው መተማመን እየቀነሰ መምጣቱ ፍርሃት እንዲሰፍንና የሰላም እጦት እንዲፈጠር አድርጓል።[25]

በአሁኑ ጊዜ የፖለቲካ ተሳትፎ በለይም ለሴቶች የዜግነት ኃላፊነት ሳይሆን አደገኛ እና ብዙውን ጊዜ አስጊ ተግባር ተደርጎ ነው የሚቆጠረው።[26] በግልም ይሁን በሲቪል ማህበራት ውስጥ የሚሠሩ ሴት የሰላም ገንቢዎች እርቅ ለማምጣት እንደሚሠሩ ሰዎች ሳይሆን እንደ ፖለቲካ ወኪሎች ተደርገው በተደጋጋሚ ስማቸው ይጠፋል።[27] ይህም ጥርጣሬ ግለሰባዊ ማንነት ከግለሰቡ ብቃት በልጦ በሚታይባቸው በጎሳ በተከፋፈሉ አካባቢዎች ላይ የጎላ ነው።[28] ከኦሮሚያ የመጡ አንድ የሰላም አስፈጻሚ ይህንን ተግዳሮት ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡- "የግጭት አፈታትን ጨምሮ ማንኛውንም የሰላም ግንባታ እንቅስቃሴ በምጀምርነት ጊዜ  ሰዎች ወዲያውኑ የፖለቲካ አጀንዳ እንዳለኝ ነው የሚጠረጥሩት። እንዲያውም ኦሮሞ ካልሆኑ ሰዎች ጋር መተማመንን መገንባት ቀላል ነው፤ ነገር ግን ከኦሮሞዎች ጋር በጣም ከባድ ነው። ሰዎች ማንነቴን እንደ ባለሙያ ብቻ አይቀበሉትም፤ ይልቁንስ  ማንነቴ ላይ በማተኮር ዓላማዬን ጥያቄ ውስጥ መክተት ይጀምራሉ።"[29]

የውጭ ሀገራትን የገንዘብ ድጋፍ መጠራጠር እና እየጨመረ የመጣው የሲቪክ ምህዳር መጥበብ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የበለጠ ይገድበዋል። በተለይም በሰብአዊ መብቶች፣ በመገናኛ ብዙኃን ነፃነትና በሲቪል ማህበረሰብ ዙሪያ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአንዳንድ ምዕራባውያን መንግሥታት መካከል ያለው ውጥረት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የሰላም ግንባታ ተዋንያንን እንቅስቃሴ እንዲቀንስ አድርጎታል። መብቶችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ላይ30የሚሰሩ ወይም ዓለም አቀፍ ድጋፍ የሚያገኙ በሴቶች የሚመሩ ድርጅቶች ብዙ ጊዜ በጥርጣሬ ይታያሉ። ይህም ወደ ከፍተኛ ቁጥጥር ያመራል፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሚናን እና ተደራሽነት ውሱን ያደርጋል፤ ብሎም አንዳንድ ጊዜ አካባቢያዊ ባለስልጣናት የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ገደብ እንዲጥሉ ወይም አሉታዊ ምላሾችን እንዲሰጡ ያደርጋል።[31] እነዚህም ተለዋዋጭ ሁኔታዎች በብዙ ግጭት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ሴት የሰላም ገንቢዎች ተቋማዊ ድጋፍ ወይም ጥበቃ ሳይደረግላቸው በምትኩ በኢመደበኛ ትስስሮች እና በግል ተአማኒነታቸው ላይ ብቻ ተማምነው እንዲሠሩ ያስገድዳቸዋል።

በተለይም ግጭት በበዛባቸው አካባቢዎች እየተስፋፋ የመጣው የጸጥታ እጦት ሴት የሰላም ገንቢዎች የሚያጋጥማቸውን አደጋ አባብሶታል። በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በትግራይ ግዛቶች ታጣቂ ኃይሎች ሰፋፊ ቦታዎችን መቆጣጠራቸውን የቀጠሉ ሲሆን ብዙውን ጊዜም ያለ ተጠያቂነት ይንቀሳቀሳሉ። ይህ የጸጥታ እጦት በሴቶች ላይ የከፋ ተጽዕኖ ያሳድራል። ብዙ ሴት የሰላም ገንቢዎች ትንኮሳ ደርሶባቸዋል፣ ማስፈራሪያ ተፈጽሞባቸዋል ወይም በአነቃቂ እንቅስቃሴያቸው ምክንያት ማህበረሰባቸውን ትተው ለመሰደድ ተገድደዋል።[32] የሕግ፣ ተቋማዊ ወይም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ መዋቅር አለመኖር ሥራቸውን አደገኛና እይታ አልባ አድርጎታል። ወንድ መሪዎች ብዙውን ጊዜ በድርድር ወይም ጥምረት በመፍጠር የጦርነት ሁኔታዎችን ማለፍ ሲችሉ ሴቶች ግን የመገለል፣ ኢላማ የመሆን ወይም ዝም እንዲሉ የመገደድ እድላቸው ሰፊ ነው። አንዳንድ ሴት የሰላም ገንቢዎች የሚያደርጉትን የዜግነት ተሳትፎ ለማደናቀፍ ሲባል ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል ወይም በቤተሰቦቻቸው ላይ ዛቻ ተፈጽሞባቸዋል። ሌሎች ደግሞ በየአካባቢያቸው የውይይት መድረክ በማዘጋጀታቸው ብቻ የስለላ ወይም ፖለቲካዊ ግብ ያለው አፍራሽ ሥራ መሥራት በሚል ተከስሰዋል።[33] በዚህም ምክንያት ሴቶች በአካባቢያዊ የሰላም ሂደት ውስጥ ያላቸው ሚና እየተበታተነና ወጥነት እያጣ ከመምጣቱም በላይ ደህንነታቸውን እና ሕጋዊነታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ በግል ግንኙነቶቻቸው ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ተገድደዋል።

ይህንን እንቅፋት ለማለፍ የሚጠቅሙ እርምጃዎች

1. *ያልተማከሉ ሴት-መር የጥበቃ ትስስሮችን ማቋቋም፡፡* መደበኛ የጸጥታ ዋስትናዎች ደካማ በሆኑበት ወይም በሌሉበት ጊዜ፣ ማህበረሰባዊ የጥበቃ ዘዴዎች የተሻለ አማራጭ ይሰጣሉ። ከደቡብ ሱዳን እና ከሰሜን ናይጄሪያ የተገኙ ስኬታማ ልምዶችን በመጠቀም በተለይም በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በትግራይ ክልሎች ውስጥ የኢትዮጵያ የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች ሴት-መር የቅድመ የማስጠንቀቂያ እና የጥበቃ ኮሚቴዎችን እንዲያቋቁሙ መደገፍ ያስፈልጋል። እነዚህ ቡድኖች በመከሰት ላይ ያሉ ስጋቶችን መከታተል፣ ጸጥታን የተመለከቱ መረጃዎችን በትክክለኛው ጊዜ በምስጢራዊ መንገዶች ማጋራት እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ አካባቢውን የመልቀቂያ እቅዶችን ማስተባበር ይችላሉ። በየአካባቢው ከሚገኙ ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት መሪዎች ጋር አጋርነት መፍጠር የቡድኖቹን ሕጋዊነት እና ተቀባይነት ሊያሳድገው ይችላል። ዓለም አቀፍ ለጋሾች እና ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም (INGO) ለእነዚህ ቡድኖች የጥበቃ እገዛ፣ የሥነልቦና ድጋፍ እና ደህንነቱ በተጠበቀ እንቅስቃሴ ላይ ባተኮረ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ይፋዊ ያልሆነ ነገር ግን የአጠቃቀም ምቹነት ያለውን የገንዘብ ድጋፍ መስጠት አለባቸው።

2. *የሰላም ግንባታ የገንዘብ አቅርቦት ውስጥ ተለዋዋጭ ሁኔታን ግምት ውስጥ ያስገባ የጸጥታ ድጋፍን ማካተት።* የሰላም ግንባታ የገንዘብ ዕርዳታዎች በለድርሻ አካላትን  ከጥቃት የመጠበቅ አገልግሎቶች (ለምሳሌ፣ አድራሻ መቀየር፣ የሕግ ድጋፍ፣ የዲጂታል ደህንነት ሥልጠና፣ ጊዜያዊ መጠለያዎች) የሚሆኑ የበጀት መስመሮችን ማካተት አለባቸው። እነዚህ እርምጃዎች ከሴት የሰላም ገንቢዎች ጋር በጋራ የተነደፉና እንደ ጾታዊ ጥቃትና ስም ማጥፋት ያሉ አካባቢያዊ አደጋዎችን ያገናዘቡ መሆን አለባቸው። የፖለቲካ ጥርጣሬን ወይም የታለሙ ጥቃቶችን ለማስወገድ የገንዘብ ዕርዳታው በአካባቢው በሚታመኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወይም በሚፈለገው አካባቢ ውስጥ ጥሩ የትስስር መረብ እና ተቀባይነት ባላቸው የድርጅቶች ህብረቶች በኩል መተላለፍ አለበት።

3. *ለታለመ ጥቃት ምላሽ ለመስጠት የሕግ ማዕቀፎችንና አሠራሮችን ማጠናከር።* በኢትዮጵያ የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት (WPS) ምህዳር ውስጥ የሚታየው ትልቅ ክፍተት ሴቶች ለተጋረጠባቸው ፖለቲካዊ ወይም ከግጭት ጋር የተያያዘ ጥቃት ተገቢ የሆነ የሕግ ጥበቃ አለመኖር ነው። ለምሳሌ፣ በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሴ ሰላም ገንቢዎችን የሚመለከቱ እንደ እንባጠባቂ ያሉ አሠራሮች ወይም ራሳቸውን የቻሉ የጥበቃ ማዕከላት ሊቋቋሙ ይችላሉ። በሴቶች የሚመሩ እንደነዚህ አይነት አካላት የሕግ ጥሰቶችን መመዝገብ፣ ከፍትሕ ተቋማት ጋር መገናኘትና ተጠያቂነት እንዲኖር መወትወት ይችላሉ። በተለይም ርቀው በሚገኙ ወይም ወታደራዊ ኃይል በበዛባቸው አካባቢዎች በሴቶች የሰላም ተዋናዮች ላይ የሚቃጡ ዛቻዎችን ለመመርመር እነዚህ አካላት በጠንካራ የፖለቲካ ፈቃደኝነት ሊታገዙ ይገባል።

4. *ለዘብተኛ ዲፕሎማሲን በመጠቀም መንግሥታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ኃይሎችን በሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት ቁርጠኝነት ላይ አሳታፊ ማድርግ ።* መንግሥታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች በኢትዮጵያ ውስጥ መሬትን በመቆጣጠር እና የአካባቢ አስተዳደርን በመቅረጽ ረገድ ያላቸውን ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት በሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት ሥራዎች ላይ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ማሳተፍ አስፈላጊ ነው። ለጋሾች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተባበሩት መንግሥታት የፖለቲካ እና የሰላም ግንባታ ጉዳዮች መምሪያ የአሠራር ስልቶችን እና የጄኔቫ የቁርጠኝነት ጥሪ ማዕቀፍን በመጠቀም መንግሥታዊ ካልሆኑ ተዋናዮች ጋር ሴቶች በሰላም ሂደቶች ውስጥ ሊደረግላቸው ስለሚገባው ጥበቃ እና ስለሚኖራቸው ተሳትፎ ሊወያዩ ይገባል። እነዚህም ውይይቶች ጉዳዩን ከውጭ እንደተጫነ ትዕዛዝ ከማቅረብ ይልቅ በአካባቢያዊ እሴቶች (ለምሳሌ ክብር፣ የህብረተሰብ ደህንነት) ዙሪያ በማዋቀር ቢያቀርቡት ተቃውሞን ሊቀንስ ይችላል። ሴት የሰላም ገንቢዎች የእነዚህን ውይይቶች አግባብ በመንደፍ ረገድ ማገዝ የሚገባቸው ሲሆን፣ በታጣቂ ኃይሎች ውስጥ ያሉ ወንዶችም እንደ አጋር ሊካተቱ ይገባል።

## 3.2 እንቅፋት 2፡ የፖሊሲ መቆየት እና የተጠያቂነት እጥረት

የቆየ እና ወቅታዊነትን ያላገናዘበ  የጾታ ፖሊሲዎች እና አስገዳጅ የሕግ ቁርጠኝነት አለመኖር በኢትዮጵያ ውስጥ ለሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እና አመራር እንቅፋት ሆነዋል። የጾታ እኩልነትን በተመለከተ በተደጋጋሚ ሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ቁርጠኝነት የተንጸባረቀ ቢሆንም 1985ቱ የኢትዮጵያ የሴቶች ፖሊሲ ጊዜ ያለፈበት እና በአብዛኛውም ያልተተገበረ ነው። ምንም እንኳን ፖሊሲውን በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውንም አይነት አድልዎ ለማስወገድ የተፈረመውን አለም አቀፍ ስምምነት (CEDAW)፣ የቤጂንግ የድርጊት መርሃ ግብር እና የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 1325 ጋር ለማጣጣም የተሻሻለ ረቂቅ ቢዘጋጅም እስካሁን እንደ ሕግ አልፀደቀም።[34] የፖሊሲው መጓተት ስርዐተ ጾታን የማስረጽን ሥራ እንዲበታተን ያደረገ ሲሆን የጾታ እኩልነትን ከሕጋዊ ግዴታዎች ይልቅ በፖለቲካዊ ፈቃደኝነት ላይ እንዲመሠረት አድርጎታል።

ይህ የሕግ ክፍተት ሴቶች በአመራርነት ሚና ረገድ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲቀንስ አድርጓል። በ2010 አካባቢ በተደረገው የፖለቲካ ማሻሻያ ወቅት የተገኙት የጾታ ሚዛናዊነትን የጠበቀ ካቢኔን እና ከፍተኛ የሴት አመራሮች መሾምን የመሳሰሉ ስኬቶችም የተፈለገውን ውጤት ሳያስከትሉ ተቀልብሰዋል። ለሴቶች የተሰጠው የ30 በመቶ የፖለቲካ ውክልናም በቋሚነት ባለመተግበሩ በሀገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ በአስገዳጅነት ተግባራዊ የሚደረግበት ሕጋዊ ዘዴ የለም። ምላሽ ሰጪዎች እንዳረጋገጡት ጠንካራ የአፈጻጸም ዘዴዎች እስከሌሉ ድረስ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ከታይታ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም።[35] የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርም ቢሆን ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ያለበት መሥሪያ ቤት ሲሆን የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ወይም በተለያዩ ዘርፎች የሚደረጉ ጾታን ያገናዘቡ ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል በቂ የፖለቲካ ተፅዕኖ የለውም።

ለሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት(WPS) ትግበራ የጸደቀ ብሔራዊ የድርጊት መርሀ ግብር (NAP) አለመኖሩ የኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1325ን ተግባራዊ የማድረግ አቅም በእጅጉ ተገድቧል። መንግሥት በ2011 ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ለማዘጋጀት ፍላጎት እንዳለው ከመግለጹም በላይ የተባበሩት መንግሥታት የሴቶች ድርጅት (UN Women) እና የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በ2012 የምክክር መድረኮችን መምራት ቢጀምሩም ሂደቱ ለውጥ  አላሳየም።[36] ይፋዊ የሆነ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በሌለበት ሴቶች በሰላም ሂደቶች ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ ጊዜያዊና በአብዛኛው በውጭ አካላት የሚመራ ይሆናል። በርካታ ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች እንዳመለከቱት፣ ይህ ክፍተት በሴቶች የሚመሩ ሲቪል ማህበራት የሰላም ግንባታ ፈንድ እንዳያገኙ፣ የተኩስ አቁም ስምምነቶች ላይ ክትትል እንዳያደርጉ እና ለሽግግር ፍትህ ስርዓቶች አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ አግዷቸዋል።

ምንም እንኳን እነዚህ ተግዳሮቶች ቢኖሩም፣ የሴቶች ድርጅቶች የሕግ ማሻሻያና ተቋማዊ ተጠያቂነትን በመጠየቅ ረገድ ግንባር ቀደም ሆነው ተሰልፈዋል። የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ኔትወርክ እና የኢትዮጵያ ሴቶች የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ትይዩ ሪፖርቶችን (shadow report) በማዘጋጀት፣ ሀገራዊ ምክክሮችን በማካሄድ እና የጾታ እኩልነት ማዕቀፎችን እንቅስቃሴ ለማበረታታት ፖሊሲ አውጪዎችን በማነሳሳት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ይህም ቀጣይነት ያለው ውትወታ የጾታ ፖሊሲ ረቂቅ ወደ መጽደቅ እንዲቃረብ እና የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት አጀንዳም በሀገራዊ ትኩረት ውስጥ እንዲቆይ አድርጓል። ክልላዊ የሴቶች ድርጅቶች እና የሕግ ባለሙያዎችም ከሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት መርሆች ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ መዋቅር ከግምት ያስገቡ ንዑስ-ሀገራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች እና የክትትል ስልቶች እንዲቀረጹ ሠርተዋል።[37] ይሁን እንጂ ስር የሰደደ የፖለቲካ ተቃውሞ፣ ውስን የገንዘብ ድጋፍ እና ቢሮክራሲያዊ መቆየት እድገታቸውን አግቶቷል። በመሆኑም ኢትዮጵያ የጾታ ፖሊሲውንም ሆነ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን በይፋ ስላላጸደቀች፤ በሰላምና በጸጥታ አስተዳደር የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችል በመንግሥት የሚመራ ሥርዓት እንዳይኖራት ሆኗል።

እነዚህ የፖሊሲ መሣሪያዎች ከፀደቁና ከተተገበሩ ተቋማዊ ተጠያቂነትን በእጅጉ ሊያሳድጉና መጠነ ሰፊ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ። መጽደቃቸውም የጾታ ተዋጽኦን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የሴቶችን አመራር ሚና ለማስጠበቅ፣ ለሰላም ግንባታ የሚውሉ ሀብቶችን ለማስገኘት እንዲሁም የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት (WPS) ጉዳዮችን በፌደራል፣ በክልልና በማህበረሰብ ደረጃ በሚገኙ አሠራሮች ውስጥ ለማካተት ሕጋዊ መሠረትን ይፈጥራል። እስከዚያው ድረስ የሴቶች ተሳትፎ በአጋጣሚ በሚፈጠሩ የፖለቲካ እድሎች ላይ ብቻ የሚመሠረት ይሆናል፤ ይህም ለውጡን ለመቀልበስ አደጋ ያጋልጠዋል።

ይህንን እንቅፋት ለማለፍ የሚጠቅሙ እርምጃዎች

1. **የተሻሻለውን ብሔራዊ የጾታ ፖሊሲ እና የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት (WPS) የድርጊት መርሃ ግብርን ማጠናቀቅና ተግባራዊ ማድረግ።** ይህም ከተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 1325 እና በሴቶች ላይ የሚደርስን አድሎ ለማስወገድ ከተፈረመው ስምምነት (CEDAW) ጋር የሚጣጣም ግልጽና አስገዳጅ የሕግ ማዕቀፍ እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህም ተቋማት የጾታ እኩልነትን በተመለከተ በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ የገቡትን ቃል ኪዳኖች ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣ በጀት እንዲመድቡና ክትትል እንዲያደርጉ የሚያስገድዱ አሠራሮችን ማካተት ይኖርበታል። ኢትዮጵያ በሰላም ግንባታና በጸጥታ ዘርፎች ውስጥ ስርዓተ ጾታን ለማስረጽ ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮችን ከተጠቀሙ እንደ ኬንያና ናይጄሪያ ካሉ ሌሎች አፍሪካዊ ሀገራት ልምድ ልትወስድ ትችላለች።

2. **የስርዓተ ጾታ ተዋጽኦን እና የአመራር ግቦችን ህጋዊነቱን በጠበቀ መልኩ ተቋማዊ ማድረግ።** ነባሮቹን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ ወይም ለአብነት ያህል የተተገበሩ የስርዓተ ጾታ ኮታዎችን በሁሉም የውሳኔ ሰጪ አካላት ውስጥ ቢያንስ ከ30-50 በመቶ የሴቶች ውክልና መረጋገጡን ወደሚያስገድዱ የሕግ ድንጋጌዎች መቀየር። እነዚህ ድንጋጌዎች በሰላም ድርድሮች፣ በሽግግር አስተዳደር አካላት እንዲሁም በፌዴራልና በክልል ፓርላማዎች ላይ ተፈጻሚ መሆን አለባቸው። የእነዚህን ሕጋዊ ዘዴዎች ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ቅጣቶችን ወይም ማበረታቻዎችን ማካተት ያስፈልጋል። የሩዋንዳ ሕገ መንግሥታዊ የኮታ ሥርዓት የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ በሕግ በማስጠበቅ ረገድ ስኬታማ ቀጠናዊ ሞዴል ነው።

3. **ስርዓተ ጾታ ላይ ትኩረት ያደረገ የገንዘብ አቅርቦትን መጨመር እና ለይቶ መመደብ።** የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች በሴቶች ጉዳይ ላይ ያተኮሩ አካላት የጾታ ፖሊሲውን እና የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነትን (WPS) ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ መጠኑ የጨመረ እና ለዚሁ አላማ ብቻ ተለይቶ የተመደበ የገንዘብ አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ። ይህም የገንዘብ አቅርቦት የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት የድርጊት መርሃ ግብሮችን፣ ጾታን ያገናዘበ በጀት አወጣጥን እና በየክልሉ የሚገኙ የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬቶች አቅም ግንባታን ጨምሮ በክልል ደረጃ ለሚደረጉ ንዑስ ሀገራዊ ተግባራት ተብሎ ተለይቶ መመደብ ይኖርበታል። ለጋሾችም በሰላምና አስተዳደር ዘርፍ ለሚንቀሳቀሱ በሴቶች ለሚመሩ ሲቪል ማኅበራት (CSOs) በቀጥታ ለበርካታ ዓመታት የሚቆይ እና ለአጠቃቀም ምቹ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት አለባቸው።

4. **አካታች፣ ቋሚ እና በርካታ ባለድርሻ አካላትን ያቀፉ የተጠያቂነት ሥርዓቶችን ማቋቋም።** የመንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን፣ የሴቶች መብት ተቋማትን፣ የሕግ ባለሙያዎችንና የክልል ተወካዮችን ያካተቱ ራሳቸውን የቻሉ/ነጻ የባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ መድረኮችን በመፍጠር የጾታ ፖሊሲውንና ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን አፈጻጸም መከታተል። እነዚህም መድረኮች ለሕግ ተገዢነትን መቆጣጠር፣ በጾታ የተከፋፈለ መረጃ መሰብሰብ፣ ይፋዊ የአፈጻጸም/የግሥጋሤ ሪፖርቶችን ማውጣትና የእርምት እርምጃዎችን መጠቆም አለባቸው። እንዲህ አይነቱ ስልት ግልጽነትን የሚጨምር እና ፖለቲካዊ ግዴለሽነትን የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ ሲቪል ማኅበረሰቡ በሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት አስተዳደር ውስጥ ያለው ሚና ተጠናክሮ እንዲቋቋም ያደርጋል።



## 3.3 እንቅፋት 3፡ ገንዘብ ነክ እንቅፋቶች እና ኢኮኖሚያዊ መገለል

ገንዘብ ነክ ጥገኝነት እና መዋቅራዊ ኢኮኖሚያዊ መገለል የሴቶችን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወኑ የሰላም ግንባታ ሂደቶች ውስጥ የመሳተፍ አቅም በእጅጉ የሚገድቡ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ እንቅፋቶች የእለተለት ወጪ የሚያጥራቸው በማህበረሰብ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ የሰላም አስፈፃሚዎች እና በድህረ-ግጭት ማገገሚያና ሀገራዊ ውይይት ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር የሚጥሩ የሲቪል ማህበረሰብ ባለሙያዎችን ጨምሮ በሁሉም ደረጃዎች ላይ የሚገኝ የሴቶች ተሳትፎን የሚጎዱ ናቸው።[38] ሴቶች ወደ ሰላም መድረኮች እንዳይሳተፉ የሚያደርጉ የኢኮኖሚ ችግሮች ካልተፈቱ ተሳትፏቸው የተገደበ፣ ለስሙ የተደረገ ወይም ዘላቂነት የሌለው ሆኖ ይቀራል።

በሰሜኑ ጦርነት በተለይም በትግራይ፣ በአማራ እና በአፋር ክልሎች የሚገኙ ሴቶች መጠነ ሰፊ መፈናቀል፣ የወንድ የቤተሰብ አባላት ሞት እና አካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ውድመት በተፈጠረበት ሁኔታ ውስጥ የቤተሰባቸው ዋና አስተዳዳሪ ለመሆን ተገደዋል። ወሎ ውስጥ በመንግሥት ኃይሎች እና በታጠቁ አካላት መካከል በተፈጠረው ግጭት ሳቢያ ሴቶች ኢኮኖሚያዊውን ጫና እንዲሸከሙ ተደርገዋል። መተዳደሪያቸው በመስተጓጎሉ እና ገበያዎች በመፍረሳቸው ምክንያት በመፈናቀል ስጋት፣ በጥቃት እና በገንዘብ ንጥቂያ መካከል ቤተሰባቸውን ከመንከባከብ በተጨማሪ ሴቶች ሌሎች ተደራራቢ ሸክሞች ገጥመዋቸዋል።[39] አንድ ከትግራይ የመጡ የቃለመጠይቁ ተሳታፊ እንደተናገሩት፣ "ጦርነትን ያለፉ ሰዎች በተለይም ባሎቻቸውን ያጡ ሴቶች ትልቁ ትኩረታቸው በሕይወት መቆየት ነው። እነዚህ ሴቶች ብዙውን ጊዜ የቤተሰቦቻቸው ራስ ሆነው መምራት እና ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል። ምግብና መጠለያን መሰል መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው ሳይሟሉ የሰላም ግንባታ ጥረቶች ላይ እንዲሳተፉ መጠየቅ እንደቅንጦት ነው የሚቆጠረው።"[40] ሀገራዊ የሰላም ግንባታ ተዋናዮች ጦርነቱ በሴቶች ላይ ያለውን ተፅዕኖ የተገነዘቡ ቢሆንም፤ ከግጭት በኋላ ባሉ ሂደቶች የሴቶችን መሪነት ለማበረታታት ኢኮኖሚያዊ የማገገሚያ ድጋፍ የሰጡት ግን ጥቂቶች ናቸው።

እንደ ኦሮሚያ እና ሶማሌ ባሉ ክልሎች ውስጥ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት ከአባዊ ልማዶች ጋር ተዳምሮ ሴቶች በአካባቢው የሰላም ጥረቶች ውስጥ እንዳይሳተፉ አግሎሏቸዋል። ሴቶች ያለክፍያ የሚሰጡት የቤት ውስጥ እንክብካቤ ጫና በስልጠና፣ በምክክር ወይም በውይይት መድረኮች ላይ እንዳይገኙ ያግዳቸዋል። አንድ የጥናቱ ተሳታፊ እንደተናገሩት "በደቡብ ምስራቅ ኦሮሚያ በተካሄደ ስልጠና ላይ፣ ምንም እንኳን ስልጠናው የሙሉ ቀን ቢሆንም ራሳቸውን ለማስተዳደር አረቄ ማውጣት ስላለባቸው እና ልጆቻቸውን ሲጠብቁላቸው ከነበሩ ሰዎች መቀበል ስለነበረባቸው ብዙ ሴቶች ቀኑን ሙሉ መሳተፍ አልቻሉም።"[41] ለመጓጓዣ የሚሆን ገንዘብ እጥረት፣ የልጆች እንክብካቤ ወይም ገቢ ከሚያስገኙ ተግባራትርቆ ለመቆየት አለመቻል ሴቶች በዘላቂነት በሰላም ሂደቶች ውስጥ እንዳይሳተፉ ያግዳቸዋል። በሶማሌ ክልልም ቢሆን አካባቢያዊ ባለሥልጣናት ሴቶችን በሰላም ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ የሚጋብዙ ብሆንም፤ በወንድ ቤተሰቦቻቸው ላይ ያላቸው የኢኮኖሚ ጥገኝነት (የትራንስፖርት አበልን ወይም ለተሳትፎ ምቹ የሆኑ መድረኮችን የመሳሰሉ ድጋፎች አለመኖር ጋር ተዳምሮ) የሴቶችን ተሳትፎ እንዲገድበው ሆኗል።[42]

በተለይም በገጠር ወይም በበቂ ሁኔታ አገልግሎት በማይገኝባቸው አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ በሴቶች የሚመሩ የሰላም ግንባታ ድርጅቶች አሁም ድረስ መዋቅራዊ የገንዘብ እጥረት አለባቸው። በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሱ አንድ የሰላም ገንቢ እንደገለጹት፣ "በአንድ በኩል የሰላም ግንባታ ጽንሰ-ሐሳብ ለአካባቢው ማህበረሰብ አዲስ ነው። ማህበረሰቡን በበቂ ሁኔታ ለመድረስ በቂ ግብዓት ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ በገንዘብ እጥረት ምክንያት በአካባቢው ያሉ ባለሙያዎች ግጭቶችን ለመፍታት የሚያግዙ ሳይንሳዊ አቀራረቦችን እና ዘዴዎችን እንዲያውቁ የሚያስችላቸውን በቂ ሥልጠና እያገኙ አይደለም።"[43] ለጋሾችም ጥልቅ የማህበረሰብ ትስስር እና አካባቢያዊ ዕውቀት ያላቸውን አዳዲስ ተዋናዮችን ትተው ትላልቅ (ብዙውን ጊዜ በከተማ ላይ የተመሠረቱ) መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይመርጣሉ።

በሀገራዊ የውይይት መድረኮች ወይም የተኩስ አቁም ስምምነትን የሚከታተሉ አካላትን በመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የሰላም ግንባታ ሥራዎች ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ሊያስቀጥል የሚያስችል የብዙ ዓመት መሠረታዊ ድጋፍ የሚያገኙ የሴቶች ድርጅቶች በጣም ጥቂት ናቸው። ዓለም አቀፋዊ የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት ማዕቀፎች ለሴት የሰላም ገንቢዎች የሚሰጡ የገንዘብ አቅርቦቶች እና ድጋፎች በየአካባቢው እንዲዳረሱ ጥሪ ቢያቀርቡም፤ የእንዲህ አይነቱ ድጋፍ ተደራሽነት አሁንም እጅግ ማዕከላዊነትን የተከተለ፣ ቢሮክራሲያዊ አሠራር የሞላበት እና በአካባቢያዊ ፍላጎት ላይ ሳይሆን ለጋሾች ለአደጋ ተጋላጭነት ባላቸው ስጋት ላይ የተመሠረተ ነው።

ለኢኮኖሚያዊ እንቅፋቶች ስልታዊ ትኩረት እስካልተሰጠ ድረስ ፍላጎት ወይም የመሪነት ብቃት በማጣታቸው ሳይሆን፣ መዋቅራዊ ቸልተኝነት በመኖሩ ምክንያት ሴቶች እየተለወጠ በመጣው የኢትዮጵያ የሰላምና ጸጥታ ሥርዓት ውስጥ ከመሳተፍ መገለላቸውን ይቀጥላሉ። ሴቶች የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ የወደፊት ዕጣ ፈንታ መቅረጽ መቻላቸውን ለማረጋገጥ፣ እነሱን ዒላማ ያደረገ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም ጾታን ያገናዘበ የሰላም የገንዘብ አቅርቦት ማዕቀፍ በአስቸኳይ ያስፈልጋል።

የቡና ለሰላም (Coffee for Peace) ውጥን ኢትዮጵያ የሴቶች ማኅበራት ኔትወርክ (NEWA) እና የኢትዮጵያ የሰላም ገንቢ ሴቶች ኔትወርክ (EWPB) ቀርጸው የሚያስተባብሩት ሰላምን በማስፈን እና ግጭትን በመከላከል ረገድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የፆታ ልዩነት ለመቅረፍ ያለመ የሴቶች ማህበረሰብ አቀፍ ንቅናቄ ነው።

ይህ ውጥን በችግሮች ላይ ለመወያየት እና አካባቢያዊ አለመግባባቶችን ለመፍታት በሚያገለገለው በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ በቆየው ቡና አብሮ የመጠጣት ባህል ላይ የተመሠረተ ነው። ይህንን ባህላዊ ልምድ በመጠቀም ሴቶች ቡና ላይ እየተጫወቱ ሐሳቦቻቸውንና ስጋቶቻቸውን እንዲካፈሉ እርስ በእርስ ይገባበዛሉ። እነዚህ ማህበረሰብ አቀፍ ውይይቶች ሴቶች በሰላምና በደኅንነት ጉዳዮች ላይ ያላቸውን የግል ፍላጎት በአካባቢያቸው ቋንቋ እንዲገልጹ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ በመሆናቸው፤ ሂደቱን ይበልጥ ውጤታማ ከማድረጋቸውም በላይ “ምዕራባዊ” ወይም በልሂቃን የሚመራ ተብሎ ገሸሽ የመደረግ ዕድሉን ይቀንሱታል።

ይህ ሥራ ከተጀመረ ጀምሮ በስምንት ክልሎችና አስራ ስድስት ወረዳዎች ላይ የተተገበረ ሲሆን እስካሁን ከሲዳማ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከምስራቅ ኦሮሚያ፣ ከሶማሌ ክልል እና ከድንበር አካባቢ ማህበረሰቦች በተውጣጡ ሴቶች መካከል በርካታ ማህበረሰባዊ እና በይነ ክላልዊ ውይይቶች ተካሂደዋል። እነዚህ ውይይቶች ሴቶች የሰላም አጀንዳዎችን እንዲያዘጋጁ፣ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ፣ የከተማ ወንጀል፣ ፖለቲካዊ መገለልና ደካማ አስተዳደር የሚያካትቱ አካባቢያዊ የግጭት መንስኤዎችን እንዲለዩና እንዲፈቱ፣ እንዲሁም ከአካባቢያዊ ባለስልጣናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲፈጥሩ አስችሏቸዋል።

ይህ ተስፋን የሰነቀ ውጥን በተለያዩ የሴቶች ቡድኖች መካከል መተማመንንና አብሮነትን በማጎልበት፣ የተዛቡ አመለካከቶችን በመፈተሽ፣ ለማህበረሰባዊ ምክር ቤቶችና አካባቢያዊ አስተዳደሮች ምክረ ሐሳቦችን እንዲያቀርቡ በማብቃት፣ የሴቶችን አመራር ለማጠናከር እንዲሁም በማህበረሰባዊ እና በሀገር አቀፍ

---

ይህን እንቅፋት ለማለፍ የሚጠቅሙ እርምጃዎች

1. በሰብአዊነት፣ በልማት እና በሰላም ሥራዎች ትስስር ውስጥ ለስርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የገንዘብ አቅርቦትን ቅድሚያ መስጠት። በተለይም በግጭት ሳቢያ የሰዎች መተዳደሪያ በወደመባቸው አካባቢዎች ለጋሾች ስርዓተ ጾታን ያገናዘበ ኢኮኖሚያዊ ማገገምን የሰላም ግንባታ ፕሮግራሞች ዋና ዓላማ አድርገው ሊያካትቱ ይገባል። ይህም ሴቶች ገቢ እንዲያመነጩ እና የዜግነት ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚደግፉ ሥራዎችን በሰብአዊነት–ልማት–ሰላም ሥራ ማዕቀፎች ውስጥ ለዚሁ ተለይቶ የተበጀተ ገንዘብ መመደብን ያካትታል። ሴቶች ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሳያጡ በውይይት ሂደቶች ውስጥ መሳተፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ የመጓጓዣ አበልን፣ የህፃናት እንክብካቤን እና የመገናኛ መሣሪያዎችን ያካተቱ ተስማሚ የድጋፍ ጥቅሎች መዘጋጀት አለባቸው።
2. ሴት-መር ጥቃቅን የንግድ ሥራዎች እና የኅብረት ሥራ ማኅበራት ላይ ኢንቨስት ማድረግ። የኢኮኖሚ አቅምን የማጎልበት ሥራዎች ከግለሰብ ሥራ ፈጠራ አልፈው በሴቶች የሚመሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን፣ የማኅበረሰብ ቁጠባ ቡድኖችን እና የእርሻ ማኅበራትን የመሳሰሉ አሰባሳቢ ሞዴሎችን መደገፍ አለባቸው። ለጋሾች እና ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (INGO) ከየአካባቢው የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች (CSO) ጋር በመተባበር ሴቶች ገቢ ከማግኘት በተጨማሪ ተጽዕኖም ይኖራቸው ዘንድ ገንዘብ ነክ እውቀትን፣ የሙያ ክህሎቶችን እና የገበያ ተደራሽነትን የተመለከተ ሥልጠና ሊሰጧቸው ይገባል። የዜጎች ተሳትፎ ሞጁሎችን በእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ ማካተት ሴቶች በሰላም መድረኮች፣ በመሬት አስተዳደር ማሻሻያ ጥረቶች እና በየአካባቢው አስተዳደራዊ መዋቅሮች ውስጥ የመሳተፍ አቅማቸውን ያጠናክረዋል።
3. ለግጭት-ጊዜ የሚሆኑ ጥቃቅን ብድሮችንና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚጣጣሙ የመተዳደሪያ ምንጮችን ተደራሽነት ማስፋፋት። ጥቃቅን የብድር ተቋማትንና የቁጠባ ቡድኖችን በመደገፍ በግጭት ለተጠቁ ሴቶች በተለይም ለተፈናቀሉ ወይም የቤተሰባቸው ዋነኛ አስተዳዳሪ ለሆኑ ሴቶች አገልግሎታቸውን እንዲያስፋፉ ማድረግ ይገባል። የተለመደው አይነት የብድር አቅርቦት ተደራሽነት በሌለባቸው ቦታዎች ላይ ለሴቶች ተብለው በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ተንቀሳቃሽ የገንዘብ አቅርቦት መላዎች፣ ተዘዋዋሪ የቁጠባና የብድር ማኅበራት እንዲሁም ሥራ ሠርተው ጥሬ ገንዘብ የሚያገኙባቸው አሠራሮች እንደ ጊዜያዊ ዘዴ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ድርቅን የሚቋቋሙ ሰብሎችን፣ ንጹሕ ኃይል ተጠቃሚ ወይም ዘላቂ የእጅ ሥራዎችን የመሳሰሉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ መተዳደሪያዎችን ቅድሚያ ሰጥቶ መደገፍ ሴቶች የኢኮኖሚ ነፃነታቸውን እንዲያጎለብቱ እና ለአካባቢው ማገገምና ችግርን የመቋቋም አቅም አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያስችላቸዋል።

4. **በሴቶች ለሚመሩ የሰላም ግንባታ ድርጅቶች የረጅም ጊዜ መሠረታዊ የገንዘብ ድጋፍ ማቅረብ።** ለጋሾች በፕሮጀክት ላይ ተመሥርቶ ለአጭር ጊዜ የሚሰጥን የገንዘብ ድጋፍ በመለወጥ በሰላምና በኢኮኖሚያዊ ፍትህ ላይ ለሚሠሩ የሴቶች ድርጅቶች ለብዙ አመታት የሚቆይ መሠረታዊ ድጋፍ መስጠት አለባቸው። ይህም ድጋፍ ድርጅታዊ ወጪዎችን እንዲሁም የዘመቻ እንቅቃሴ፣ የአመራር ልማት እና የውትወታ ሥራዎችን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ለአጠቃቀም ምቹ የሆነ የገንዘብ ድጋፍን ያካትታል። የገንዘብ ድጋፉ ስለየማህበረሰቡ ጠለቅ ያለ እውቀት ካላቸው አካባቢያዊ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር መተማመን ላይ ተመሥርቶ በሚፈጠር አጋርነት አማካኝነት መቅረብ ይኖርበታል። ከተቻለም ደግሞ ሴቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች፣ የጊዜ ሠሌዳዎች እና የአሠራር ስልቶችን የተመለከቱ ውሳኔዎች መወሰናቸውን ለማረጋገጥ አሳታፊ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥ አካሄድ መከተል ይገባል።

## 3.4 እንቅፋት 4፡ ነጻነት ገዳቢ የስርዓተ ጾታ ደንቦች እና ማህበራዊ መገለል

ሥር የሰደዱ አባዊ ደንቦች እና አድሏዊ የስርዓተ ጾታ አመለካከቶች አሁንም ድረስ ሴቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄዱ የሰላም ግንባታ ሂደቶች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርጉ እያደናቀፉ ይገኛሉ። እነዚህ በተዋረድ በየትውልዱ ተጠናክረው የሚተገበሩ ደንቦች ሴቶችን በቤት አካባቢ ላይ ብቻ እንዲወሰኑ ከማድረግ ባለፈ በማህበረሰብ አመራር፣ በሕዝባዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና በግጭት አፈታት ረገድ ያላቸውን ተሳትፎ እና ተጽዕኖ ይቀንሳሉ። በተለይም የባህላዊ እምነቶች ከባህላዊ አስተዳደር መዋቅሮች ጋር በእጅጉ በተሳሰሩባቸው በገጠራማ እና በግጭት በተጠቁ አካባቢዎች ጉዳቱ የከፋ ነው።[44]

በአማራ ክልል በወሎ አካባቢ፣ የሥራ ክፍፍል ጾታን መሠረት ባደረጉ ማህበራዊ ግዴታዎች በእጅጉ ይወሰናል። የሴቶች ኃላፊነት የቤት ውስጥ ሥራ እና የልጆች እንክብካቤ ብቻ እንዲሆን ሲጠበቅ፣ ፍትህ፣ አመራር እና የግጭት አፈታት ግን የወንዶች ሚናዎች ተደርገው ይወሰዳሉ።[45] አንዲት ቃለ መጠይቅ ሰጪ እንደገለጹት፣ "ምንም እንኳን የእስልምና ሃይማኖት የሚከለክለው ባይሆንም በ...ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ባህላዊ ግዴታ ሴቶችን ለቤተሰባቸው እና ለልጆቻቸው እንክብካቤ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ በመሆኑ ሴቶች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው በሰላም ግንባታ ሥራዎችላይ እንዳይሳተፉ ያደርጋቸዋል።"[46] ይህ ሥር የሰደደ አመለካከት ሴቶችን እንደ 'አባጋር' ባሉ የሽማግሌዎች ሸንጎ በአካባቢው የሚነሱ ግጭቶችን በሚፈቱበት ባህላዊ የሰላም ማስፈኛ መዋቅሮች ውስጥ ከመሳተፍ ያግዳቸዋል። እነዚህ ሸንጎዎች ወንዶች ብቻ የሚሳተፉባቸው መድረኮች በመሆናቸው በማህበረሰብ አስተዳደር ውስጥ የወንዶችን የበላይነት የሚያጠናክሩ ናቸው።[47]

ተረት እና ምሳሌዎች እንዲሁም ፈሊጦች የጾታ ልዩነትን ማስተጋባትን እና ማስጠበቅን ቀጥለዋል። ለምሳሌ በሶማሌ ክልል የሚነገረው "የሴት ሻርፕ ዛፍ አይቆርጥም" የሚለው አባባል የሴቶችን አቅም እና ተፅዕኖን ለማሳነስ ጥቅም ላይ ይውላል።[48] ሌላው "የሴት ልጅ የጠባችው የጡት ወተት እሷው ጋር ወተት ሆኖ ይቀራል፤ ወንድ ልጅ የጠባው ወተት ግን አእምሮውን ይመግባል" የሚለው ምሳሌ ደግሞ ማህበረሰቡ ሴቶችን አመራር፣ ፍርድ ወይም ስትራቴጂ ከሚጠይቁ ሚናዎች በማግለል በውስጠ ታዋቂ ስለወንዶች የአእምሮ የበላይነት ያሳደረውን እምነት የሚያሳይ ነው።[49] እነዚህ ፈሊጦች የቋንቋ ቅርሶች ብቻ ሳይሆኑ፤ የሴቶችን ተሳትፎ ኢተፈጥሮአዊ ወይም አጉራዘለል የሆነ ድርጊት አድርገው በመቁጠር በሰላም ግንባታ ላይ መዋቅራዊ እንቅፋቶችን ይፈጥራሉ።

በኦሮሚያ ቦረና ዞን የሚገኙ አካባቢያዊ ባህሎች መሠረት፣ የሰላም ሂደቶች ተአማኒነት እንዲኖራቸው የወንድ ሽማግሌዎችን እውቅና እና ተሳትፎ ይጠይቃሉ። ሴቶች የሚያደርጉት አስተዋፅዖ ኢመደበኛ እውቅና ያገኘ ቢሆንም እንኳን ተቋማዊነት እና ሕጋዊነት የላቸውም።[50] በዚህም ምክንያት በሽምግልና ወይም በድርድር ላይ ጎላ ያለ ሚና ለመጫወት የሚሞክሩ ሴቶች ለከፍተኛ ማህበራዊ ትችት አልፎ ተርፎም በግል ሕይወታቸው ላይ ለሚቃጣ አደጋ ይጋለጣሉ። ከሶማሊ ክልል የመጣች አንዲት ሴት የሰላም አስፈፃሚ በግል ሕይወቷ ያጋጠማትን በይፋ በመናገሯ ማሸማቀቅ እንደደረሰባት ገልፃለች። "በሶማሊ ባህል ሴቶች ሰውነታቸውን በልብስ እንደሚሸፍኑ ሁሉ ችግሮቻቸውን መደበቅ ይጠበቅባቸዋል" ብላለች። አክላም "ግልጽ ሆኜ በመናገሬ ገመናዬን እንዳጋለጥኩ ተቆጥሮ፤ - እብድ እና ሀጢያተኛ ተብያለሁ።"[51]

ሴቶች ተጨባጭ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ኖሯቸው እና በጦርሜዳ ተሰልፈው ተዋግተው እንኳን፤ ግጭት ካበቃ በኋላ የሚኖራቸው ሚና ግን ችላ ይባላል። በትግራይ በሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶች በሰሜን ኢትዮጵያ በተካሄደው ጦርነት[52] ውስጥ የተሳተፉ ቢሆንም፤ በሰላም ድርድሩ ወይም በመልሶ ግንባታ ሂደቶች ውስጥ አልተካተቱም። አንዲት ትግራዋይት ሴት እንደተናገሩት፣ "ሴቶች የነጻነት ታጋይ መሆናቸው እና በጦርነት ውስጥ በንቃት መሳተፋቸው የተለመደ ነው፤ በትግራይ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወታደሮች ሴቶች ሲሆኑ፤ ለወታደሩ ምግብ ከማቅረብ በተጨማሪ በቀጥታ በውጊያም ውስጥ ይሳተፋሉ። ሆኖም ግን ሰላምን በመገንባት ረገድ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ከሰላም መድረኮች ይገለላሉ። ይህም መገለል በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ነው። ጦርነቱ ካለቀ በኋላ ትኩረቱ ወደ ሀብት እና የስልጣን ጉዳዮች ተቀየረ። ሴቶች ብዙውን ጊዜ ፖለቲካዊ የኃላፊነት ቦታዎችን ወይም በሰላም ውይይት ውስጥ የሚሳተፉባቸውን እድሎች ለማግኘት ይቸገራሉ። ወንዶች ብዙውን ጊዜ  ምሽት ላይ እንደ መጠጥ ቤት ባሉ ኢመደበኛ የመገናኛ ቦታዎች ይሰባሰባሉ፤ ሴቶች ደግሞ እንዲህ አይነት ቦታዎች እንዳይገኙ ባህሉ ይከለክላቸዋል። በዚህ መንገድ ከውሳኔ አሰጣጥ ቦታዎች መገለላቸው በሰላም ሂደቶች ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በእጅጉ ይገድበዋል።"[53] በዚህም ምክንያት መደበኛ እና ኢመደበኛ የማግለያ ስርዓቶች እርስ በእርስ እየተደጋገፉ በአጠቃላይ ሴቶችን ማለት ይቻላል ከቁልፍ የሰላም ግንባታ ሂደቶች አግልለዋቸዋል።

እነዚህ የማግለል ተግባራት ባህላዊ እንዲሁም ተቋማዊ ናቸው። በየክልሉ የሚገኙ ሴቶች የሴቶችን የመሪነት ሚና መደገፍ ያልተቻለው ባለው መዋቅራዊ ውድቀት ሳቢያ እንደሆነ ይናገራሉ። ከኦሮሚያ የመጣች አንዲት የሰላም ገንቢ እንዲህ ስትል ገልጻለች፣ “[አንዲት ሴት] በዘርፉ ላይ የተረጋገጠ እውቀት ኖሯት በሰላም ግንባታ ሥራ ላይ ብትሳተፍ እንኳን  ተቀባይነት አታገኝም። ሴቶችን በስልታዊ መንገድ የሚያገለው ባህል በተዘዋዋሪ መንገድ ነው የሚንጸባረቀው። እንደ ሴት፣ በሰላም ግንባታ ሰፊ ልምድ ቢኖርሽም እንኳን እድሎች አይሰጡሽም ወይም እውቅና አታገኝም። ሥርዓቱ አይረዳሽም፤ የወንድ የበላይነት ያለው ደግሞ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ብቻ አይደለም፤ በሁሉም ቦታ ሰርጾ የገባ ጉዳይ ነው። የሰላም ግንባታ እና የግጭት አፈታት ሚናዎችን በተመለከተ ቅድሚያ የሚሰጠው ለወንዶች ነው።”[54] ሴቶች ለመደራጀት፣ ጥረታቸውን ለማጠናከር እና ሕጋዊነትን ለማግኘት የሚያስችሏቸው የገንዘብ ምንጮች፣ የትስስር መረቦች እና መድረኮች ውሱን መሆናቸው ብዙውን ጊዜ እነዚህን እንቅፋቶች ይበልጥ ያወሳስባቸዋል። ዓለም አቀፉ የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት አጀንዳ ትርጉም ያለው አካታችነት ከታይታ ተሳትፎ ባለፈ  ሴቶችን የሚያገልሉ ማህበራዊ ደንቦች እና የኃይል መዋቅሮች ላይ ጭምር ለውጥ ማድረግ እንደሚያስፈልግ በግልጽ ያስቀምጣል።

ዓለም አቀፍ ተዋንያን፣ ለጋሾች እና የኢትዮጵያ ተቋማት የሴቶችን ፖለቲካዊ አቅም የሚያሳንሱ የባህላዊ ደንብ ማዕቀፎችን መጋፈጥ አለባቸው። ይህም የሰላም ሂደቶች ከመነሻው ጀምሮ ስርዓተ ጾታን ያካተተ ንድፍ እንዲኖራቸው ማድረግን፣ አካባቢያዊ በሴቶች የሚመሩ ተግባራትን መደገፍን እና ኢ-መደበኛ በሆነ የሰላም ግንባታ ሥራ ላይ የሚሳተፉ ሴቶችን ድምጽ አጉልቶ ማስተጋባትን ያጠቃልላል። እነዚህ ለውጦች እስካልተደረጉ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ የሰላም ሂደቶች ያልተሟሉ፣ ቁመናቸውም አድሎአዊ፤ ውጤታቸውም ደካማ ይሆናሉ።

ይህንን እንቅፋት ለማለፍ የሚጠቅሙ እርምጃዎች

1. አባዊ ደንቦችን የሚያደፈርስ ምህዳርን መፍጠር። የሴቶችን የቤት ውስጥ ሚናዎች፣ በሃይማኖት የተደገፉ አድሎዎች እንዲሁም ሴቶች ድምጻቸው እንዲታፈን የሚያስገድዱ የስርዓተ ጾታ ግዴታዎች የተመለከቱ ሥር የሰደዱ እምነቶችን በንቃት መታገል ያስፈልጋል። በተለይም ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ መሪዎች የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ወሰን በሚያሰምሩባቸው ሁኔታዎች ጋር በተገናኘ ለጋሾች እና ሲቪል ማህበራት እንቅፋት የሆኑ ደንቦችን ከመቃወም ወደኋላ ማለት የለባቸውም። ፕሮግራሞች በሚቀረጹበትም ጊዜ ጎጂ የሆኑ አመለካከቶችን ከመቀየር አኳያ መነደፍ አለባቸው - ለምሳሌ ባህላዊ የውይይት መድረኮችን በገንዘብ በመደገፍ፣ ሃይማኖታዊ መርሆችን በሴታዊነት መነጽር አይቶ አዳዲስ ፍቺዎች የሚሰጡበትን ሁኔታ በመደገፍ፣ ወይም ሴቶች በሰላም ሂደቶች ላይ ጎልቶ የሚታይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በመርዳት። የወንድ አጋሮችን፣ የሃይማኖት ምሁራንን እና ባህላዊ መሪዎችን ማሳተፍ ለውጡ ከማህበርሰቡ ውስጥ እንዲመጣ በማድረግ ረገድ ሊያግዝ ይችላል።
2. ሴቶች በሰላም ግንባታ ውስጥ የመሪነት ሚና የሚጫወቱበትን የረጅም ጊዜ እቅድ ማቀድ። አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጡ ስልጠናዎች ወይም ለታይታ ብቻ የሚደረግ አካታችነት በቂ አይደለም። ለጋሾች እና ሀገራዊ ተዋንያን የሴቶችን በራስ መተማመንን እና ማህበረሰባዊ እውቅናን እያዳበሩ በሰላም ግንባታ፣ በሽምግልና እና በድርድር ክህሎቶች የሚያስታጥቋቸውን በሚገባ የተዋቀሩ የረጅም ጊዜ የአመራር ልማት ፕሮግራሞች ለመቅረጽ መሥራት አለባቸው። ይህም ከሴቶች ጋር ወደ ፖለቲካዊ እና ልማዳዊ ምህዳሮች መግባትን፣ ተስማሚ የሆነ የምክር እና የስልጠና ድጋፍ መስጠትን እና ሴቶች ድምፃቸውን አጉልተው የሚያሰሙባቸውን አማራጭ የመሪነት መድረኮችን መፍጠርን ያጠቃልላል። በኢትዮጵያ ያሉ ሴት የሰላም ገንቢዎች ብዙውን ጊዜ ይህን ሥራ የሚጀምሩት ኢ-መደበኛ በሆኑ ማህበረሰባዊ የግጭት አፈታት መድረኮች ላይ ነው። እነዚህ መነሻ ነጥቦች ሀገራዊ የውይይት መዋቅሮችን፣ የፌደራል የሰላም ጽህፈት ቤቶችን እና ክልላዊ የእርቅ ኮሚሽኖችን ከመሳሰሉት መደበኛ ዘዴዎች ጋር መተሳሰር አለባቸው። ሴቶች መካተታቸው ብቻ ሳይሆን በውሳኔ አሰጣጥ ቦታዎች ላይ በቋሚነት መቆየታቸው ለውጥ ከማምጣት አንጻር ወሳኝ ነው።
3. ህዝባዊ የለውጥ ዘመቻዎችን በየአካባቢው ማካሄድ እና ማህበረሰባዊ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ። የስርዓተ ጾታ ደንቦችን ለመለወጥ የሚተላለፉ መልዕክቶች በየአካባቢው መሠረት የሚጥሉ እና ከአካባቢያዊ አውዱ ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው። የተግባቦት ስትራቴጂዎችም አድሎአዊ ደንቦችን የሚፈትሹ እና ሴት የሰላም ገንቢዎችን የሚያወድሱ አካባቢያዊ ቋንቋዎችን፣ ፈሊጦችን፣ ሃይማኖታዊ ምልክቶችን እና ተረታዊ ወጎችን ማካተት አለባቸው። የተከበሩ ሴት ሽማግሌዎችን፣ ከጦር ሜዳ የተመለሱ ሴት ተዋጊዎችን፣ ሴት አስታራቂዎችን እና የሃይማኖት መሪዎችን አጉልቶ ማሳየት የሴቶችን በፖለቲካ ምህዳር ውስጥ መገኘት እንዲለመድ ሊያደርግ እና ስልጣን የወንዶች ብቻ ነው የሚሉ ምልከታዎችን ሊያስተጓጉል ይችላል። አዎንታዊ ልዩነቶችን ለማንጸባረቅ ሲባል እነዚህ ዘመቻዎች የሴቶችን አመራር የሚደግፉ ወንዶችን ማሳየት አለባቸው። አካባቢያዊ ሲቪል ማህበር ድርጅቶች፣ ሬዲዮ ጣቢያዎች እና የወጣቶች የትስስር መረቦች እነዚህን ጥረቶች እንዲመሩ ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል፤

ይህም ተአማኒነትን፣ ትክክለኛነትን እና ተደራሽነትን ያረጋግጣል።

4. **በባህላዊ እና በመደበኛ የሰላም መዋቅሮች ውስጥ የጾታ እኩልነትን በተመለከተ ተጠያቂነትን ተቋማዊ ማድረግ።** ስለሴቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ የተቀመጠውን መመዘኛ ከ30 እስከ 50 በመቶ እንዲሆን ከፍ የማድረግ ሥራ ሴቶች በመድረኮች ላይ ከመገኘት ባለፈ ተፅእኖ እንዲያሳድሩ ከማድረግ ጋር ተጣምሮ መሠራት አለበት። ኮታውም በሀገር አቀፍ እና በክልላዊ የሰላም ኮሚሽኖች፣ በባህላዊ የግጭት አፈታት ምክር ቤቶች (እንደ አባጋር ወይም ገዳ ጉባኤዎች ያሉ) እና በሀገራዊ ውይይት እና ድርድር ሂደቶች አማካኝነት በሚፈጠሩ አዳዲስ የሽግግር አካላት ውስጥ ሁሉ መዘርጋት አለት። ለጋሾች እና የመንግሥት አካላት በሰላም ግንባታ ሁሉም ደረጃዎች ላይ የሴቶችን ተሳትፎ የሚለኩ የስርዓተ ጾታ ተጠያቂነት ማዕቀፎችን በጋራ መፍጠር አለባቸው - ይህም ከአጀንዳ አወጣጥ እስከ ሀብት አጠቃቀም ያለውን ሂደት ሁሉ ይሸፍናል። ሲቪል ማህበረሰቡም ትግበራውን በመከታተል እና ተዋንያንን ከሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት አጀንዳዎች አንጻር ተጠያቂ በማድረግ እንዲሁም በሕግ፣ በፖሊሲ እና በባህል



## 4. ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ሚናዎቻቸውን እውቅና በማይሰጡ እና በሚያገልሉ መደበኛ ሂደቶች ጥላ ሥርም እንኳን ሆነው ከጥንትም ችግሮችን የመቋቋም፣ መከፋፈልን የማስወገድ፣ ማህበረሰባቸውን የመደገፍ እና ሰላምን የማጎልበት ሥራዎችን ሲሠሩ ኖረዋል። ምንም እንኳን ተከታታይ ፖለቲካዊ ማሻሻያዎች የላቀ አካታችነትን እንደሚተገበሩ ቃል ገብተው የነበረ ቢሆንም ሴቶች አሁንም የሰላም ድርድር ከሚካሄድባቸው፣ ውሳኔዎች ከሚሰጡባቸው እና የስልጣን ክፍፍል ከሚከናወንባቸው መድረኮች በአመዛኙ እንደተገለሉ ናቸው። መገለላቸው የአጋጣሚ ነገር አይደለም፤ በአባዊ ደንቦች፣ በገንዘብ አቅም እጦት፣ በፖሊሲ ቸልተኝነት እና ፖለቲካ ተሳትፎን በሚቀጣ የጸጥታ ከባቢ ውስጥ ተተክሎ መዋቅራዊ የሆነ ነው።

ይህ ሪፖርት ኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች በሰላም ግንባታ ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚገድቡ ሦስት ተያያዥ እንቅፋቶች እንዳሉ ያሳያል፡ እነዚህም ሴቶች በጓዳ ተወስነው እንዲቀሩ የሚያደርጉ ሥር የሰደዱ ማህበራዊ ደንቦች፣ የሴቶችን እንቅስቃሴ እና ጊዜ የሚገድብ ኢኮኖሚያዊ ችግር፣ እንዲሁም የሴቶችን መካተት ችላ የሚሉ ወይም በንቃት የሚያደናቅፉ ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ ማዕቀፎች ናቸው። እነዚህ አዳዲስ ተግዳሮቶች አይደሉም። ሆኖም የሀገሪቱ ወቅታዊ ቀውስ በይበልጥ እንዲባባሱ ያደርጋቸዋል። በግጭት ውስጥ ያለፉ ማህበረሰቦች በአሁኑ ሰዓት የበለጠ ፍትሃዊ፣ ወካይነት ያለው እና አካባቢያዊ ባለቤትነቱ የተረጋገጠ ሰላም እንዲሰፍን እየጠየቁ ነው።

እነዚህ ሁሉ እንቅፋቶች ቢኖሩም፣ በመላ ኢትዮጵያ ያሉ ሴቶች የመሪነት ሚናቸውን ለመጫወት የማንንም ፈቃድ እየጠበቁ አይደሉም። በኦሮሚያ በቡና ሰዓት ከሚደረጉ ውይይቶች፣ አዲስ አበባ ውስጥ እስከሚከናወኑ የሕግ ውትወታዎች ድረስ፣ ሴቶች ድርድር ለማካሄድ የሚሆኑ አማራጭ መድረኮችን እየፈጠሩ፣ ማህበራዊ ትስስርን እያጠናከሩ እና የፖለቲካ ተዋንያንን ተጠያቂ እያደረጉ ነው። እንደ ቡና-ለ-ሰላም፣ እንነጋገር፣ እና በትግራይ እና ሶማሌ ክልሎች የሚከናወኑትን ህዝባዊ ንቅናቄዎች የመሳሰሉ ሥራዎች ለአካታች የሰላም ግንባታ ሥራ ግሩም ምሳሌዎች ናቸው። እንደነዚህ አይነቶቹ ጥረቶች ለሀገራዊ ማገገም እንደ ተጨማሪ ወይም ደጋፊ ሥራ ሳይሆን መሠረታዊ መሆናቸው እውቅና ሊሰጠው ይገባል።

ከታይታ ባለፈ እውነተኛ አካታችነትን ለማረጋገጥ ሴቶች ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን የሰላም መሃንዲሶችም ጭምር መሆናቸው ታውቆ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። ይህም የጾታ ተዋጽኦን ተግባራዊ የሚያደርጉ የሕግ ማሻሻያዎችን፣ ለሴት-መር ድርጅቶች የሚሰጥ የገንዘብ አቅርቦትን እና ሴቶች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የመሪነት ሚና እንደሚጫወቱ ዜጎች የሚገጥሟቸውን አደጋዎች ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ የስርዓተ ጾታ ትብነት ያላቸው የጥበቃ ስትራቴጂዎችን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ የሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት (WPS) ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር(NAP)ም በአስቸኳይ ተጠናቆ እና በፖለቲካዊ ቁርጠኝነት፣ በተቋማዊ የገንዘብ ድጋፍ እና የሲቪል ማህበረሰቡ የክትትል ሥራ እንዲሠራ በሚያስችሉ አሠራሮች ተደግፎ መተግበር አለበት።

ኢትዮጵያ ውስብስብና አስቸጋሪ የሽግግር ወቅት እያሳለፈች ባለችበት ሁኔታ ውስጥ ሴቶችን ማካተት የፍትሃዊነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ሰላምን የሚያሰፍን ቅድመ ሁኔታ ነው። የሴቶችን ድምጽ፣ ልምድና አመራር ከፍ ማድረግ የሰላም ሂደቶችን ሕጋዊነት ከማጠናከሩም በላይ ሀገሪቱን ከግጭት ወደ ለውጥ ለማሸጋገር የሚያስፈልገውን ማህበራዊ መሠረት ይገነባል።

## አባሪ፡ የጥናቱ ሥነዘዴ

ይህ ጥናት በሰላም ሂደቶች ውስጥ ሴቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚያግዱ እንቅፋቶችን ለማለፍ የሚጠቅሙ ውጤታማ ልምዶችን ለመለየት እና ለመረዳት የሚያስችል ምርመራ ላይ የተመረኮዘ የጥናት ዘዴን ተጠቅሟል። ከውስብስብነቱ እና በርእሰ ጉዳዩ ላይ ከዚህ ቀደም የተከናወኑ ጥናቶች ውሱን ከመሆናቸው አንጻር ይህ አካሄድ ጥልቅ ምርመራ ለማድረግ ምቹ ሆኖ ተገኝቷል። በቁልፍ ተዋናዮች እና በባለ ድርሻ አካላት ላይ ባተኮረ መልኩ እንቅፋቶቹን እና በመላው ኢትዮጵያ ከተከናወኑ የተለያዩ ሥራዎች የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ለመመርመር በርካታ የአንድ ጉዳይ/ተግባር ጥናት ስትራቴጂ ጥቅም ላይ ውሏል። ሰፋ ያለ ተፈጻሚነትን ለማረጋገጥም፣ ማህበረሰባዊ ግጭቶችን፣ ክልላዊ የተገንጣይ ቡድኖች እንቅስቃሴዎችን እና ተነጻጻሪ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ፖለቲካን ጨምሮ ተመሳሳይ የግጭት አውዶችን ከሚጋሩ የብሔር ብዝኃነት ካላቸው ክልሎች የመጡ ሰዎች ተመርጠዋል። ይህም ሴቶች በሰላም ሂደቶች ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ ወካይነት ያለውን ግንዛቤ የሚሰጥ ሆኖ ተገኝቷል። ጥናቱ ዝርዝር መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሰነዶች ግምገማን፣ ጥልቅ ቃለመጠይቆችን እና የትኩረት ቡድን ውይይቶችን (FGDs) በመጠቀም ኳሊታቲቭ የጥናት ዘዴን ተከትሏል። የሰነዶች ዳሰሳው ቁልፍ የሰላም ውይይቶችን እና ብሔራዊ የውይይት ጥረቶችን ጨምሮ ባለፉት 6 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶች የተመሩ የሰላም ሥራዎችን ተንትኗል። የተገኘው መረጃም በየርእሰ ጉዳዩ ተከፋፍሎ ውይይት ተደርጎበታል።

በጾታ፣ በቦታ፣ በእድሜ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በገጠር/በከተማ ነዋሪነት እንዲሁም በትምህርት ደረጃ ከተሰባጠሩ ናሙናዎች ግንዛቤ ለማግኘት የቁልፍ የመረጃ ሰጭዎች ቃለ መጠይቆች (KII) እና የትኩረት ቡድን ውይይቶች (FGDs) ተካሂደዋል። የተለያዩ አመለካከቶችን ለማግኘት ሲባል በትኩረት ቡድን ውይይቶች ላይ ሁለቱም ጾታዎች ተሳታፊ ሆነዋል። ተመራማሪዎቹም በሰላም ግንባታ እና ሴቶችን በማብቃት ሥራ ውስጥ ያላቸውን ልምድ በመጠቀም የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን፣ የመንግሥት ባለስልጣናትን እና የሙብት ተሟጋቾችን በጥናቱ ውስጥ አካተዋል። መረጃ የተሰበሰበው ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ግጭቶችን እና የሰላም ሂደቶችን ካስተናገዱ አምስት ክልሎች ማለትም ከትግራይ፣ ከአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ከሶማሊ እና ከአዲስ አበባ ነው።

በእያንዳንዱ ክልል የፖሊሲ አውጪዎችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎችን፣ የማህበረሰብ መሪዎችን እና የሰላም ግንባታ ባለሙያዎችን ያሳተፉ አራት አራት ቃለመጠይቆች ወይም በድምሩ 20 ቁልፍ መረጃ ሰጪዎችን (6 ወንዶች፣ 14 ሴቶች) ያሳተፉ ቃለ መጠይቆች ተካሂደዋል። የተለያዩ አመለካከቶችን ለመሰብሰብ በድምሩ 19 ተሳታፊዎች (5 ወንዶች፣ 14 ሴቶች (2 አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ)) የተገኙባቸው ሁለት የትኩረት ቡድን ውይይቶች አዲስ አበባ ውስጥ የተካሄዱ ሲሆን በውይይቶቹም ላይ ሴት የሙብት ተሟጋቾች፣ የአካባቢያዊ ማህበረሰብ አባላት እና የሰላም ግንባታ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

# የጀርባ ማስታወሻዎች


1. Semir Yusus, *Drivers of Ethnic Conflict in Contemporary Ethiopia*, Institute for Security Studies, 9 December 2019, https://issafrica.org/research/monographs/drivers-of-ethnic-conflict-in-contemporary-ethiopia.
2. International Crisis Group, "Ethiopia's Tigray War: A Deadly, Dangerous Stalemate", 2022, https://www.crisisgroup.org/africa/horn-africa/ethiopia/ethiopias-tigray-war-deadly-dangerous-stalemate.
3. Ángel Olaran, "600,000 Civilians Died in Two Years of War in Ethiopia", Centre d'Iniciatives Solidàries, February 2, 2023, https://isolidaries.org/en/600000-civilians-died-in-two-years-of-war-in-ethiopia; Harvard Humanitarian Initiative, Ethiopia Peace & Justice Survey, 2023, https://hhi.harvard.edu/publications/ethiopia-peace-justice-survey-2023.
4. International Crisis Group, *Finding a Path to Peace in Ethiopia's War-Torn Tigray*, Report No. 184, 11 February 2021, https://www.crisisgroup.org/africa/horn-africa/ethiopia/167-finding-path-peace-ethiopias-tigray-region.
5. Human Rights Watch, *Ethiopia: Atrocities in Oromia Amid Conflict*, 9 March 2023.
6. International Crisis Group, *Ethiopia's Amhara Region: Tackling a Government Crisis*, Briefing No. 186, 4 August 2023.
7. Abel Eshetu Gebremedhin, "Impact of the Civil War in Ethiopia on the Export Economy in Oromia, Amhara, and Tigray, Borkena", 29 May 2024, https://borkena.com/2024/05/29/impact-of-the-civil-war-in-ethiopia-on-the-export-economy-in-oromia-amhara-and-tigray.
8. United Nations Office for the Coordination of Humanitarian Affairs (OCHA), *Ethiopia Humanitarian Situation Update, January–December 2024*, https://www.unocha.org/publications/report/ethiopia/ethiopia-humanitarian-situation-update-january-december-2024.
9. OCHA, *Ethiopia Humanitarian Snapshot,* May 2024, https://www.unocha.org/publications/report/ethiopia/ethiopia-humanitarian-snapshot-may-2024.
10. OCHA, *Ethiopia Situation Report,* 13 December 2024, https://www.unocha.org/publications/report/ethiopia/ethiopia-situation-report-13-december-2024.
11. Wilson Center, "Gender-Based Violence and the Tigray Conflict in Ethiopia: A Path to Accountability and Resolution", 31 July 2023, https://www.wilsoncenter.org/blog-post/gender-based-violence-and-tigray-conflict-ethiopia-path-accountability-and-resolution.
12. UN Women, "In Ethiopia, a Rapidly Changing Humanitarian Crisis Demonstrates the Need for a Flexible Response", October 2023, https://africa.unwomen.org/en/stories/news/2023/10/in-ethiopia-a-rapidly-changing-humanitarian-crisis-demonstrates-the-need-for-a-flexible-response.
13. Harter, Fred, "HIV soars after a deadly war in Ethiopia's Tigray. Trump's aid cuts aren't helping", Associated Press News, 26 March 2025, https://apnews.com/article/ethiopia-hiv-aids-tigray-war-health-usaid-8c3275003f6894aa943cd81dacdf18cd.
14. UN Women, Humanitarian Gender Alert: Women, Peace and Security and Humanitarian Action in Context of Ethiopia, 3 (2023), https://africa.unwomen.org/en/digital-library/publications/2023/05/humanitarian-gender-alert-women-peace-and-security-and-humanitarian-action-in-context-of-ethiopia.
15. United Nations, *Women's Rights in Political Transitions,* 2013, https://www.ohchr.org/en/stories/2013/08/womens-rights-political-transitions.
16. Adam Moe Fejerskov and Lars Engberg-Pedersen, *Violence Against Women in Ethiopia*, Relief Web, 2024.

17. United Nations Development Programme (UNDP), *Outcome Document: Policy Dialogue Forum – Integrated Approach to Amplifying the Voices of Women in Peacebuilding & Reconciliation in Ethiopia*, 2022, https://www.undp.org/ethiopia/publications/outcome-document-policy-dialogue-forum-integrated-approach-amplifying-voices-women-peacebuilding-reconciliation-ethiopia

18. UN Women, *Abridged Ethiopia Country Gender Profile*, July 2024, p. 45, https://africa.unwomen.org/sites/default/files/2024-07/abridged_version-ethiopia_country_gender_profile.pdf.

19. UN Women, *Women, Peace and Security in Africa: 2023 Continental Results Report*, 2023.

20. Oxfam International, *No Peace Without Women: Gender Justice and the Peace Process in Ethiopia*, 2023.

21. *Addis Standard*, "News: Women-Led Civil Societies in Ethiopia Call for Sustained Dialogue with Armed Groups, Inclusion of Women in Peace Talks", 8 February 2024, https://addisstandard.com/news-women-led-civil-societies-in-ethiopia-call-for-sustained-dialogue-with-armed-groups-inclusion-of-women-in-peace-talks/.

22. Ibid.

23. UN Women, *Ethiopian Country Gender Equality Profile*; UN Women and Ministry of Women, Children, Youth, and Social Affairs, "Engaging CSOs in Developing Ethiopia's National Action Plan on Women, Peace, and Security", 16 September 2024, https://ethiopia.un.org/en/283988-engaging-csos-developing-ethiopia%E2%80%99s-national-action-plan-women-peace-and-security.

24. Ibid.

25. International Crisis Group, *Managing Ethiopia's Unsettled Transition*, Africa Report No. 322, 21 February 2023.

26. Focus Group Discussion 2, Addis Ababa, 1 December 2024.

27. Mulugeta Gebrehiwot Berhe, *A Peace Deal with Pitfalls: The Pretoria Agreement and Its Implementation Challenges*, PRIO Policy Brief, 2023.

28. Key Informant Interview 1, Addis Ababa, 24 October 2024.

29. Key Informant Interview 2, Addis Ababa, 28 October 2024.

30. Freedom House, *Freedom in the World 2023: Ethiopia*, 2023. https://freedomhouse.org/country/ethiopia/freedom-world/2023.

31. Ibid.

32. Key Informant Interview 5, Dukem, 13 November 2024.

33. Ibid.

34. UN Women Africa, *Developing a National Action Plan on Women, Peace and Security in Ethiopia*, 2022, https://africa.unwomen.org/en/digital-library/publications/2022/11/developing-a-national-action-plan-on-women-peace-and-security-in-ethiopia.

35. Focus Group Discussion 1, Addis Ababa, 1 December 2024.

36. UN Women, *Ethiopia Country Gender Profile.*

37. UN Women, *Developing a National Action Plan*, 13–14.

38. Ibid.

39. Key Informant Interview 8, Dassie, 16 November 2024.

40. Key Informant Interview 3, Makale, 4 November 2024.

41. Key Informant Interview 5, Dukem, 13 November 2024.

42. Key Informant Interview 11, Jigjiga, 20 November 2024.

43. *Ibid*.

44. UN Women, *Ethiopia Country Gender Profile.*

45. Key Informant Interview 7, Kombolcha, 16 November 2024.

46. Key Informant Interview 4, Makale, 4 November 2024.

47. Ibid.

48. Key Informant Interview 10, Jigjiga, 19 November 2024.

49. Ibid.

50. Kassaye Berhanu, “Women’s Role in Peace Building and Conflict Resolution in Ethiopia: The Case of Borana Oromo Women”, *International Journal of Community and Cooperative Studies* 3, no. 3 (2015): 1–10.

51. Key Informant Interview 9, Jigjiga, 18 November 2024.

52. Meskerem Fisseha, “Women Fighters of Tigray: Their Roles and Challenges in the Tigray People’s Liberation Front (TPLF)”, *Review of African Political Economy*, 2021.

53. Key Informant Interview 4, Makale, 4 November 2024.

54. Key Informant Interview 6, Chancho, 13 November 2024.

EUROPEAN INSTITUTE OF PEACE

European Institute of Peace
Rue des Deux Eglises 25
1000 Brussels, Belgium
www.eip.org
info@eip.org